# ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል በየሰንበት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማስተማሪያ የተዘጋጀ

መስከረም 1993 ዓ.ም

ርእስ

መግቢያ

1. **ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት**

መግቢያ

- የክርስትና እምነት መሠረተ ትምህርት
- ምሥጢረ ኩነት አምላካዊ
- ፍጥረተ ዓለምና የፈጣሪ ሠራዒ መጋቢነት
- የሰው ልጅ ተፈጥሮና ኑሮው
- ተስፋ ድኅነት፣ ድኅነት፣ ምሥጢረ ድኅነት
  ምክንያተ ድኅነት
- ድኅነት በዘመነ ብሉይና በዘመነ ሐዲስ
- የእምነትና የአምልኮ ቀኖና አፈጻጸም
  በብሉይና በሐዲስ ኪዳን
- አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት
- ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን
- ስለ ክርስትና እምነት የተከፈለ መሥዋዕትነት
  በዘመነ ሐዋርያት፣ በዘመነ ሰማዕታት፣ በዘመነ ሊቃውንት
- ነገረ ማርያምና ነገረ ቅዱሳን

2. **ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን**
   - ምሥጢረ ጥምቀት
   - ምሥጢረ ሜሮን
   - ምሥጢረ ቁርባን
   - ምሥጢረ ክህነት
   - ምሥጢረ ንስሐ
   - ምሥጢረ ቀንዲል
   - ምሥጢረ ተክሊል

3. **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ**
   - የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት
   - ዘመነ መናፍቃን
   - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
     ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

4. ***ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን***
    - የቤተ ክርስቲያን አተካከልና አሠራር
    - ሥርዓተ ጥምቀት
    - ሥርዓተ ሜሮን
    - ሥርዓተ ቁርባን
    - ሥርዓተ ንስሐ
    - ሥርዓተ ክህነት
    - ሥርዓተ ተክሊል

5. **<u>የስብከት ዘዴ</u>**
    - ለሰባኪው የሚያስፈልገው
    - የስብከት ዓይነቶች
    - ስብከት የሚሰጥባቸው ቦታዎች
    - ለተለያዩ ምእመናን የሚሰጡ ስብከቶች
    - ስብከትና ፖለቲካ
    - ስብከትና ኦርቶዶክሳዊ ጠባዩ
    - በዕድሜ ደረጃ ከፋፍሎ ማስተማር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# መግቢያ

ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊው ጥበብ መጻሕፍት ከፍ ያለ ድርሻ ያበረክታሉ፡፡ ሰዎች ከበጎው የሚተባበሩበትን፣ ከክፉው የሚርቁበትን የዕለት ተግቦራቸውን የሚያከናውኑበትን ምሥጢር ይገልጣሉ፣ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም አንዳንድ የነገረ ሃይማኖት ሊቃውንት መጻሕፍትን «መንገድ አመልካቾች» በማለት ይጠሯቸዋል፡፡

የጥንት አባቶቻችንም ይህን በመረዳት መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥበብ የሚያስጨብጡ መጻሕፍትን በብዙ ድካም ብራና ፍቀው፣ቀለም በጥብጠው ጽፈው አቆይተውልናል፡፡ ይህም አባቶቻችን ከእግዚአብሔር ያገኙትን ሃይማኖት፣ ጥበብ እንድንይዝ አድርጎናል፡፡ ቅደስት ቤተ ክርስቲያናችንንም የመጻሕፍት ማኅደር ለመሆን አስችሏታል፡፡

መጽሐፍ ማዘጋጀት ብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ያለበት ቢሆንም «በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል» እንዲሉ ሊቃውንት በጉባኤያቸው ያስተማሩት ትምርት ሳይጠፋ ሳይቆነጸል ለልጆቻቸው እንዲደርስ በማሰብ ጸሐፊ አዘጋጅተው አስጽፈው ለዛሬው ትውልድ አቆይተዋል፡፡ አሁን ያሉ አባቶቻችንም ይህንኑ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ማኅበረ ቅዱሳንም በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን ያሏት ሊቃውንት በተለያዩ ጊዜያት የሚያስተምሩት ትምህርት ለምእመናን እንዲዳረስ፣ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ በማለት መምህራን በቃል ያስተማሩትን፣ በአንዳንድ ሽቶች ያሰፈሩትን በማሰባሰብ በመጻሕፍት መልክ እንዲቀርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት የተባለው መጽሐፍ ከላይ እንደተጠቀሰው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በካህናት ማሰልጠኛዎች፣ በሰንበት ት/ቤቶች፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መንፈሳዊ ጉባኤያት ያስተማሩት ትምህርት ውጤት ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ የተካተቱት ትምህርቶች አብዛኞዎቹ በተለያዩ መምህራን በሽት መልክ የቀረቡ ነበሩ፡፡ በመሆኑም ለአያያዝ የማይመቹ፣ ለጉዳት የተጋለጡና ረጅም ጊዜ ለማቆየትና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ የማይመቹ ናቸው፡፡ ሽቶቹንም

በጊዜው እያባዙ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረጉ ለከፍተኛ የገንዘብ፣ የጊዜና የጉልበት መባከን የሚዳርጉ ናቸው:: እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ፣ የሊቃውንቱ ትምህርት በትምህርታቸው እንዲተላለፍና መጪው ትውልድ ቀደምት አባቶቹን በትምህርታቸው እንዲያውቅ ለማድረግ ትምህርቶቹን በጽሑፍ መልክ ማቅረቡ ታላቅ አስተዋጽዖ አለው::

ማኅበረ ቅዱሳን ዓላማ አድርጎ የተነሳው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ነገረ ሃይማኖትንና፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከማሳወቅ አንፃር ይህ መጽሐፍ ለተቋማቱ በማስተማርያነት መልክ የቀረበ ነው:: በመሆኑም በሁሉም ተቋማት በሚገኙ መንፈሳዊ ጉባኤያት መስጠት ያለባቸውን ትምህርቶች የካተተ በመሆኑ ተማሪዎቹ ተመርቀው ሲወጡ ስለ ነገረ ሃይማኖታቸው አንድ ዓይነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል::

መጽሐፉ ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት፣ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና የስብከት ዘዴ የሚሉ ትምህርቶችን በውስጡ ያካተተ ነው:: በመጽሐፉ ውስጥ ከተካተቱ ትምህርቶች መካከል አንዳንዶቹ በሌሎች ሊቃውንት በመጽሐፍ መልክ የቀረቡ ቢሆንም በሁሉም ቦታ ያሉ ተማሪዎች የሚያገኟቸው በመሆኑና ለማስተማርያነትም ጉልህ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ በከፊል በሚያዘጋጃቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች ተገኝተው በማሰልጠን፣ ከመጻሕፍቶቻቸውም በከፊል ወስደን በዚህ መጽሐፍ አካተን እንድናሳትም የተባበሩንን መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን የጠ/ቤተ ክህነት ም/ዋና ሥራ አሥኪያጅ፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማዊ፣ ሊቀካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየን በልዑል እግዚአብሔር ስም እናመሰግናቸዋለን:: በተለያዩ ቦታ የምትገኙ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ውድና ብርቅ የሆኑ አባቶቻችን በብዙ ጥረትና ድካም አዘጋጅተዋቸው የቀሩትን ትምርቶች በማሰባሰብ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር የሚታተምበትንና ለትውልዱ አገልግሎት የሚሰጡበትን መንገድ እንድታመቻቹ አደራ እንላለን::

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን::

# ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት

በመልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን
የጠ/ቤተ ክርህነት ም/ዋና ሥራ አሥኪያጅ

## መግቢያ

**«ወዘእንበለ ተአምኖሰ ኢይትከሃል ያሥምርዎ፤ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻልም»**

ዕብ.11÷6

በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረው የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር ያለው ግንኙነት የአባትና ልጅ ያህል ወይም ከዚያ በላይ ቅርበት ያለው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖርና እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚቻለውም በእምነት እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል፡፡ ከዚያም በምን ዓይነት እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት እንደሚቻል ከራሱ ከቅዱስ መጽሐፍ ቃልና እንዲሁም ከዘመነ ብሉይና ከዘመነ ሐዲስ ቅዱሳን ምእመናን ሕይወት ሁሉንም ዓይነት ትምህርት ማግኘት ይቻላል፡፡

የክርስትና እምነት የእግዚአብሔር ወዳጅነቱ ከተመሰከረለት ከአብርሃም እምነት የቀጠለ ትክክለኛ ሃይማኖት ስለሆነ በእምነትና በምግባር አብርሃምን መስሎና አህሎ በመኖር እግዚአብሔርን ማስደሰት የሚቻለው በዚህ እምነት ነው፡፡ ለዚህ እምነት መሠረቱ ብሉይ ኪዳን ስለሆነ ትምህርተ «ክርስትናን» ከሥር መሠረቱ ጀምሮ መማር የሚቻለው ከብሉይ ኪዳን መነሣት ሲቻል ነው፡፡

# የክርስትና እምነት መሠረተ ትምህርት

### የሰው ልጅ ስለ እግዚአብሔር ኑባሬ ያለው ዕውቀት ፍጹምነት

በመሠረቱ ዓለም በራሱ  የተገኘና በራሱ የሚኖር ወይም ያለ  አስገኝ  በራሱ የተገኘና ያለሠራዒና መጋቢ በራሱ የሚኖር ሥነ ፍጥረት አይደለም፤ ለተፈጥሮው አስገኝ ለኑሮው ሠራዒ መጋቢ፣ ለጉዞው መነሻና መድረሻ አለው፡፡  ከባሕር ወለል በላይ በተን መልክ ወደ አየር የወጣ ውኃ በዝናም መልክ ተመልሶ ወደ ምድር

እንደሚወርድና ከዚያም ወንዝ ፈጥሮ ወደ ባሕር ወለል እንደሚጓዝ የሰው ልጅም እንዲሁ መነሻው መድረሻው የሆነ ተጓዥ እንደሆነ በቃለ እግዚአብሔር ምስክርነትና በእምነት ማወቅ ይቻላል። የማያውቅም ይህን ሊያውቅ ይገባል። ለዚህ ዕውቀትና እምነት ታዲያ ሥር መሠረቱ በቅድሚያ ለሚያየውም ሆነ የማይታየው ዓለም ፈጣሪና ሠራዒ መጋቢ እንደ አለው ማወቅና ማመን ነው።

## የዕውቀት ምንጭ ሥነ ፍጥረት

<table>
<tr><td>ስለ ሥነፍጥረት የሃይማኖት ትምህርት ቤትነት ማስረጃ ጥቅስ</td><td>«ወዘሰ ኢያስተርአይ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም፣ ይትዐወቅ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ = ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ይታወቃል።» ሮሜ.1÷ 21</td></tr>
<tr><td>«እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩሃል፤ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ፣ ይነግሩሃል፤ ወይም ለምድር ተናገር፤ እስዋም ታስተምርሃለች፤ የባሕርም ዓሦች ይነግሩሃል፤ የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንደ አደረገ። ከእነዚህ ሁሉ የማያውቅ ማነው? የሕያዋን ነፍስ ሁሉ፣ የሰውም ሁሉ ነፍስ በእጁ ናት» ዮሐ.12÷7-10።</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>«ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሠራ፣ ከሰማይም ዝናምን፣ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንንም በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም።» የሐዋ.14÷17።</td></tr>
<tr><td colspan="2">የማይታየውና የማይዳሰሰው አምላክ በሚታይና በሚዳሰስ ሥራው የሚታይና የሚዳሰስ ያህል ራሱን ለሰው ልጅ እንዲህ ግልጽ በማድረጉ ሥነ ፍጥረት ለፈጣሪ ህልውና እውነትነት አስተማማኝ የዕውቀት ምንጭ ሆኖ እንደኖረ ወደፊትም ይኖራል። ፈጣሪ በአርአያውና በአምሳሉ ከፈጠረው የሰው ልጅ ጋር ቃል ለቃል በመነጋገር ያደረገው ቀጥታ ግንኙነት</td></tr>
<tr><td>ስለ ሰውና እግዚአብሔር የቃል ለቃል ንግግር ማስረጃ ጥቅስ፤</td><td>« እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ሲል አዘዘው÷ ከገነት ፍሬ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከምታሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርስዋ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» ዘፍ.2÷16</td></tr>
<tr><td>«እግዚአብሔርም ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው÷ ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም</td><td></td></tr>
</table>

| | |
|---|---|
| *ሙሏት፡፡» ዘፍ.*9÷1 | |
| | *«እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፤ ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ እባርክሃለሁ፤ ለበረከትም ሁን፡፡» ዘፍ*12÷1፡፡ |
| *«እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ሁሉን እንደሚችል አምላክ ተገለጥሁ፤ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም ነበር፡፡» ዘጸ.*6÷2፡፡ | |
| | *«እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር፡፡» ዘጸ.*33÷11፡፡ |
| *«እርሱም አለ÷ ቃሌን ስሙ፤ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፣ ወይም በሕልም አነጋግረዋለሁ፣ ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤ እሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው፡፡ ዘኁ.*12÷6-8፡፡ | |
| *እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር በራእይ፣ በሕልም፣ በገሃድ ያደረገው የቃል ለቃል ንግግር የህልውናውነን እውንነት ይበልጥ ግልጽ ያደረገው ስለሆነ እግዚአብሔርን ማወቅ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነበት ጊዜ የለም፡፡* | |
| *በእግዚአብሔር መስተናግርነት የተነገሩና የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት የምስክርነት ቃል* | |
| «ሰማያትን የፈጠረና የሠራ፣ ምድርንና በውስጧ ያለውን ያጸና፣በእርስዋ ለሚኖር ሕዝብ እስትንፋስን፣ ለሚንቀሳቀሰውም መንፈስ የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡፡» ኢሳ.42÷5፡፡ | |
| | *«ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ፤ ይህ የሚታየውም ከሚታይ እንዳልሆነ በእምነት እናውቃለን፡፡» ዕብ.*11÷2፡፡ |
| «ዓለሙንና በእሱ የለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤ እሱ ሕይወትንና እስትንፋስን፣ ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም፡፡ እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉት ዘንድ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፤ የተወሰኑ ዘመናትንና ለሚኖሩበት ሥፍራም ዳርቻን አበጀ፤ ከሁላችን የራቀም አይደለም፤ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን፤ እንኖራለንም፡፡» የሐዋ.17÷24-29፡፡ | |
| | *«ከዚህ ከንቱ ነገር ሰማይና ምድርን ባሕሩንና በእርሱ ያለውን ሁሉ ወደፈጠረ ወደሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንግልን እንሰብካለን፡፡ የሐዋ.*14÷15-17፡፡ |

<table>
<tr><td>«አንተ ግን በተማርክበት ነገር ጸንተህ ኑር፤ ከማን እንደ ተማርከው ታውቃለህና፤ ከሕፃንነትህ ጀምሮ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃልና- የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡» 2ኛ ጢሞ.3÷14-17፡፡</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>«ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ /በሕግ በአምልኮ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው/ እግዚአብሔር እንዳለና ለሚፈልጉትም ዋጋን እንደሚሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልጋል፡፡» ዕብ.11÷6፡፡</td></tr>
<tr><td>«እርሱን ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አምናችሁ የእምነታችሁን ፍጻሜ፣ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ የማይነገር ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ ይላችኋል፡፡» 1ጴጥ.1÷8-10፡፡</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="2">የቅዱስ መጽሐፍ ቃል ለእግዚአብሔር ህልውና ብቻ ሳይሆን ለፈጣሪነቱ ሠራዒ መጋቢነቱም ሕያው ምስክር ስለሆነ በታማኝ ምስክርነቱ ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="2" align="center">በደኃራዊ ዘመን ሰው የሆነው የወልደ እግዚአብሔር አምላካዊ ቃል</td></tr>
<tr><td></td><td>«ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፣ ከወልድም በቀርና ወልድ ለገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም፡፡» ማቴ.11÷27፡፡</td></tr>
<tr><td> እግዚአብሔር በልጁ ራሱን ስለመግለጡ ማስረጃ ጥቅስ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ኅበረ ትንቢትና በብዙ ኅብረ አምሳል ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ በዚህ ዘመን ደግሞ ሁሉን ወራሽ በአደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን፡፡» ዕብ.1÷1-3፡፡</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>«የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደሆነ ያውቃሉ፤ የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነሱም ተቀበሉት፤ ከአንተም ዘንድ እንደ መጣሁ በእውነት አወቁ፤ አንተም እንደላክኸኝ አመኑ፡፡» ዮሐ.17÷8-9፡፡</td></tr>
<tr><td>«መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳ የለም፤ በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እሱ ገለጠው እንጂ፡፡» ዮሐ.1÷18፡፡</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="2">በዚህ ሁሉ ምስክርነት እግዚአብሔር ራሱን ግልጽ ያደረገ አምላክ ስለሆነ ከሆነ ጀምሮ የሰው ልጅ ለራሱም ሆነ ለሌላው ሥነ ፍጥረት አንድ ፈጣሪና ሠራዒ መጋቢ እንደአለው ያውቃል፡፡ በማወቁም ለዚህ እውነተኛ አምላክ አምልኮቱን ሲገልጽ ኑሯል፤ ይኖራልም፡፡</td></tr>
</table>

# ምሥጢረ ኩነት አምላካዊ

# አካላዊ ምሥጢረ ኩነት

እግዚአብሔር መንፈስ ነው /ዮሐ.4÷24/:: በመሆኑም የሚታይና የሚዳሰስ አምላክ አይደለም:: ከአካሉ ርቀት የተነሣ ከቶ በእይታና በዳበሳ ህልውናውን ለማረጋገጥ አይቻልም:: እንዲህ ስለሆነ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በሚዳሰስ ሥራውና በሚሰማ ቃሉ ራሱን ግልጽ ያደረገ ስለሆነ ህልውናው ከሰው የተሰወረ አይደለም:: በመሆኑም ቅዱስ መጽሐፍ «ጨለማን መሰወሪያው አደረገ» /መዝ.16÷11/ በሚል ቃል ኅቡዕነቱን «እንወቅ» እናውቅም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፤ እንደወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን» /ሆሴ.6÷3/ የሚል ኃይለ ቃል ደግሞ ክሡትነቱን ይገልጣል:: በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ኅቡዕ ሲሆን ክሡት፤ ክሡት ሲሆን ኅቡዕ አምላክ እንደሆነ ይታመናል::

ከዚህም ጋር በተለይ ንጹሕ ልብ ላላቸው ሃይማኖተኞች ራሱን በይበልጥ ግልጥ እንደሚያደርግ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል:: ማቴ.5÷6:: ሆኖም የፈጣሪን ምሥጢረ ኩነት ከዚህ ስፋትና ጥልቀት አልፎ ለመመራመር አቅሙ ከሰው አእምሮ በላይ ስለሆነ የሰው ልጅ በአሳቡ የፈለገውን ያህል ቢንጠራራ የዚህን ዕውቀት ጣራ መንካት አይችልም:: ይህ ከሆነ ደግሞ የሰው ልጅ እንደ ፍጡርነቱ የታየውንና የተገለጠሉትን ያህል ተረድቶ ከአቅሙ በላይ የሆነውን በአንክሮ የማያልፍ አማኒ ቢሆን አቅሙን አዋቂ በመሆኑ ይመሰገንበታል፤ አቅምን ማወቅ ሊቅነት እንጂ አላዋቂነት አይሆንምና::

# ባሕርያዊ ምሥጢረ ኩነት

እግዚአብሔር በባሕርዩ፡-

- ቅዱስ - ዘሌ.19÷2፣ አሳ.6÷3 ፣1ጴጥ.1÷15
- ጻድቅ - 1ሳሙ. 2÷2፣ 2ጢሞ.4÷8፣ ራዕ.16÷7
- ሁሉን ቻይ - ዘፍ. 17÷1፣ 18÷14፣ ኢሳ.40÷26፣ ሉቃ.1÷37
- ሁሉን አዋቂ - መዝ.24÷10፣ 38÷2፣ ኤፌ.4÷6
- በሁሉ ቦታ ምሉዕ - መዝ.139÷6-11፣ ዮሐ.1÷9-11
- ዘለዓለማዊ - መዝ.89÷1-3፣ ኢሳ.44÷6፣ ያዕ.1÷11
- ጥበበኛ - መዝ.103÷24፣ ሮሜ.11÷33

-ቸር፣መሐሪ፣ ይቅር ባይ- ሰቆ.ኤር.2÷22፣ መዝ.102÷8፣

ሮሜ.2÷4፣ ዮና.4÷2-11

- ፈታሂ በጽድቅ - ኢሳ.9÷1-5፣ 60÷10፣ ኤር.18÷8-12፣

31÷36-38፣

ወዘተ. የሆነ አምላክ ነው። ይህ ባሕርይ የእግዚአብሔር ልዩ ገንዘብ ቢሆንምበአርያውና አምሳሉ የፈጠረው ሰውም በጸጋ የሚታደለው ቅድስና፣ጽድቅ፣ከሃሊነት፣ዕውቀትና ጥበብ፣ቸርነትና መሐሪነት ወዘተ አለ።

«እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ»ዘሌ 19÷2፣1ጴጥ.1÷15

## አምላካዊ ስየሜ

እግዚአብሔር ለባሕርዩና ግብሩ ተስማሚ የሆነ ስም ያለው አምላክ ነው። ፈጣሪ ራሱን ለሰው ልጅ በቅድሚያ ግልጽ ያደረገው የከሃልነቱን ምሥጢር ስለሆነ /ዘጸ.6÷3/ በመጀመሪያ «ኤልሻዳይ/ኤልሻዳይ» /ከሃሊ/ በሚል ስም ራሱን ገለጠ። ዘፍ.16÷1፣ ሕዝ.10÷5።

ቀጥሎም በባለሚሉ በሙሴ ቃል ስለ ስሙ ተጠይቆ በሰጠው መልስ

- ዘሃሎ ወይሄሎ /አህያ፣ ሽራህያ/ የነበረና የሚኖር
- «አምላከ አብርሃም፣ አምላከ ይስሐቅ፣ አምላከ የዕቆብ» የሚሰው የተጸውዖ ስም የዘለዓለም መጠሪያው እንዲሆን መፍቀዱን አረጋገጠ። ዘጸ.3÷14። ከዚያም በመቀጠል «ይሆዋ» ወይም «ያህዌ» የሚሰውን ስመ -ተጸውዖ ለሰው ልጅ ግልጽ ስላደረገ በዚህ ታላቅ ስም ሲጠራና ሲመለክ ይኖራል። ዘጸ.3÷2-6፣ 17÷15።

«ይሆዋ» ወይም «ይህዌ» የሚለው ቃልወደ እግዝ ሲመለስ «እግዚአብሔር» በሚል ቃል ተተክቶ ይታያል። ይህ ቃል የዓለም ፈጣሪና ሠራዒ መጋቢ ከነባሕርዩና ግብሩ ማለት እሱነቱ በጠቅላላ ከነማንነቱና ምንነቱ የሚገለጽበት ታላቅ ስያሜ ስለሆነ በአይሁድ ቤተ ክህነት በዓመት ውስጥ በተወሰነ የምህላ ጊዜ፣ ያውም በሊቀ ካህናቱ ካልሆነ በቀር የማንኛውም ጊዜና ሰዓት በሚካሄድ የግልም ሆነ የማኅበር ጸሎት ላይ አይነሣም። በዚህ ፈንታ በዘወትር ጸሎት እግዚአብሔር የሚጠራው

-አምላክ /አምላኬ (ኤሎሄ/ ኤሎሂም)

- ጌታ /ጌታዬ (አዶን/ አዶኒ/አዶናይ)

- ልዑል (ኢሲዮን/ኤል ኤሲዮን)

በሚል የተጸውዖ ስም ነው፡፡ ከዚህም ጋር እነዚህን የተጸውዖ ስሞች «እግዚአብሔር» /ያህዌ/ ከሚለው ዐቢይ ስም ጋር በማጣመር

- ጌታ እግዚአብሔር መዝ.7÷1፣ ሕዝ.2÷4፡፡
- ሕያው እግዚአብሔር ዳን.5÷18፡፡
- ልዑል እግዚአብሔር ዳን.6÷20፣ ዘፍ.14÷18-23፡፡
- እግዚአብሔር አምላክ ዘጸ.2÷4፡፡

እያሉ መጥራት የታወቀ ልማደ መጽሐፍ ሆኖ ይታያል፡፡

ከዚህ ላይ በጥልቀት ማስተዋል የሚያስፈልገው እግዚአብሔር በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ሕዝብ የሚታወቀውና የሚጠራው ራሱ ለራሱ ባወጣው ስም መሆኑን ነው፡፡ በሰው የወጣለት ስያሜ ቢኖር እንኳ እግዚአብሔርነቱን ከነአምላካዊ ባሕርዩና ግብሩ የሚገልጥ እንጂ ከዚያ ውጭ ወይም ከዚያ ያነሰ ትርጉም ያለው አይደለም፤ ሊሆንም አይገባውም፡፡

ከዚህም ጋር ቅዱስ መጽሐፍ «አምላክ ፈጣሪ፣ ጌታ ከሃሊ፣ ሠራዒ መጋቢ፣ አዳኝ ፈታሂ፣ ወዘተ...» በሚል ቃል አምላካዊ ግብሩን፣ «ሕያው፣ ዘለዓለማዊ፣ የነበረና የሚኖር፣ ቸር፣ መሐሪ፣ ይቅር ባይ» ወዘተ... በሚል ሌላ ቃል ደግሞ አምላካዊ ባሕርዩን ሲገልጽ «እግዚአብሔር የሚለው ስያሜ ግን እሱነቱን ከነባሕርዩና ግብሩ የሚገልጽበት ቃል በመሆኑ ይህ ስም ለፈጣሪ የመጨረሻው ስመ ተጸውዖ እንደሆነ ሁሉም ዓለም በየእምነቱ ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም በዚህ ስም አምልኮቱን ሲገልጽ ኑሯል፣ ይኖራልም፡፡

ይህ እንዲህ ሲሆን ፈጣሪ በሰው ዘንድ የሚጠራበት ስያሜ ሁሉ እሱነቱን በትክክል ለመግለጽ ወይም ለመጥራት የማያስችል አናሳ ቃል እንደሆነ አድርገው የሚያስቡ ወገኖች መኖራቸው አልቀረም፡፡ ይህ አባባል እውነት ከሆነ እግዚአብሔር የሚመለከው እሱን እንደ እሱነቱ በትክክል ለመጥራት በማያስችል ስም ነው እንደማለት ሊሆን ነው፡፡ ለመሆኑ እሱ ራሱ ለራሱ ያወጣው ስም ራሱን እንደእሱነቱ ሊገልጥ እንደማይችል ማሰብም ሆነ መናገር እንዴት ይቻላል? ይህ ከሆነማ አባባሉ ከእሱ በላይ ስለእሱ አውቃለሁ ማለት ሊሆን ነው፡፡

በሌላ አንጻር በእርግጥ ለሰው የሚነገር ቃል ሁሉ ለፈጣሪ ሲነገር የፈጣሪን ባሕርይና ግብር ለመግለጽ በቂ ቋንቋ ላይሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ምሉዕ ሲሆን ቅዱስ መጽሐፍ ግን እንደውሱን ፍጡር «መጣ፣ ሄደ፣ ወጣ፣ ወረደ» ወዘተ... ሲል ይገኛል፡፡ ይህ ዓይነቱ ቋንቋ ታዲይ ሰውኛ እንጂ እግዚአብሔርኛ አይደለም፡፡

ለምሳሌ ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለ ቃል ሥጋ መሆን ሲመሰክር «ብርሃን ወደ ዓለም መጣ» ካለ በኋላ «በዓለም ነበረ» ይላል። ዮሐ.1÷9። ወንጌላዊው በዓለም ላይ ያለውን አምላክ «መጣ» ሲል የተናገረውና «መጣ» ያለውን ደግሞ እንደገና መልሶ «በዓለም ነበረ» ያለው በመሳሳት አይደለም። ወንጌል የተሰበከው በሰውኛ ቋንቋ ስለሆነ መጀመሪያ በዓለም ላይ ያለውን አምላክ እንደውሱን ፍጡር «መጣ» አለ። በዓለም ላይ ምሉዕ እንደገና «በዓለም ነበረ» የሚል እግዚአብሔርኛ ቃል መልሶ አዳነው። «ንባብ ይገድላል፣ ትርጓሜ ግን ያድናል» /2ቆሮ.3÷6/ ተብሎ እንደተጻፈ ገድሎ ማዳንም ልማደ መጽሐፍ ስለሆነ አያስተችም።

አሁንም ይህን የሞተ ንባብ ሕያው ለማድረግ ሲያስፈልግ «መጣ» የሚለውን ቃል «ታየ፣ ተገለጠ» ብሎ በመተርጎም ማዳን ያስፈልጋል። እግዚአብሔር በየትኛውም ዓለም ምሉዕ ስለሆነ «መጤ» ሊባል ከቶ አይገባውምና።

ከዚህ በተረፈ እግዚአብሔር የሚጠራበት ስያሜ እሱን እንደ እሱነቱ ለመጥራት በቂ አይደለም ማለት ለስሙ የሚሰጠውን ክብር ለሰው ልጅ በስም ያስተዋወቀው ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ስለስሙ ብቃትና ፍጹምነት አዋቂው ራሱ ባለቤቱ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ከእሱ በላይ ስለእሱ አውቃለሁ ማለትም ትክክለኛ ዕውቀት አይሆንም።

## ፍጥረተ ዓለምና ምሥጢረ ተፈጥሮ

### ፍጥረተ ዓለም

«ፍጥረተ ዓለም» የሚለው ቃል ራሱ የፈጣሪን መኖር የማያመለክት ዓለም አቀፍ ቋንቋ ነው። በእርግጥ ዓለም የአንድ ብቸኛ ፈጣሪ ግሩም ድንቅ ሥራ መሆኑ ለሰው ልጅ ግልጽ የሆነው ከተፈጥሮ ጋር ስለሆነ የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማም የዚህን አምላካዊ ተግባር አፈጻጸም ለማዘከር እንጂ የአዲስ ዕውቀት ግኝት ለማስተዋወቅ አይደለም። ዓለም የተፈጠረው በተለያየ መልክና ጠባይ፣ መጠንና ቅርጽ እንደመሆኑ ሥነ ፍጥረት የፈጣሪን መኖር ብቻ ሳይሆን ከሃሊነቱን ጭምር የሚገልጽ ተአምራዊ ተግባር ነው። ይህንም በዓይን አይቶ መረዳት ስለሚቻል ብዙ ትውውቅ የሚያስፈልገው አይሆንም። በዚህ ዓይነት ኅብረ ተፈጥሮ የተገኘውን ዓለም በዝርዝር ለመግለጽ ከመሞከር ይልቅ «ሕያውና ግዑዝ፣ ረቂቅና ግዙፍ፣ ሰማያዊና ምድራዊ፣ ጊዜያዊና ዘለዓለማዊ» በሚል የጥቅል ስም ማስተዋወቅ የዓይነቱን ወይም የኅብሩን ብዛትና ምንነት በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል ይሆናል።

## ምሥጢረ ተፈጥሮ

ሥነ ፍጥረት አሁን ያለውን ህልውና ያገኘው በሁለት መንገድ ሲሆን ይህም በትርጓሜ ቤት ዘይቤ

- እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ
- ግብር እምግብር በመባል ይታወቃል፡፡

-«እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ» ማለት ካለመኖር ወደ መኖር ወይም «ከኢምንት ወደምንት» ወይም አስቀድሞ ካልተገኘ ነገር የተገኘ ማለት ነው፡፡ ይህ ዓለም እንዴት እንደተገኘ በዝርዝር ለመረዳትም የአሪት ዘፍጥረትን የመጀመሪያ ምዕራፍ መመልከት ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም፡-

- «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፣ ይህ የሚታየውም ከሚታይ እንዳልሆነ በእምነት እንናገራለን፡፡ ዕብ.11÷3፡፡
- «እሱ ተናግሯልና ተፈጠሩ፣ እሱ አዘዘ፣ ጸኑም፡፡» መዝ.32÷9 የሚለውንና የመሳሰለውን ቃለ መጽሐፍ በመመልከት በዚህ በኩል ያለውን የዕውቀት አድማስ ማስፋት ይቻላል፡፡
- ግብር እም ግብር ማለት ደግሞ አስቀድሞ ከተፈጠረ ነገር የተገኘ ማለት ነው፡፡

## የተፈጥሮ ስለምን

ዓለም እንዴት እንደተፈጠረ ለማዘከር ያህል ይህን ሐተታ ማድረግ እንዳስፈለገ ሁሉ ስለ ምንነቱም አዘክሮ ማለፍ እንዲሁ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው ለክብሩ መግለጫ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል፡፡ /ኢሳ.43÷7/፡፡ «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጣሉ» /መዝ.18÷1/ የሚለው ቃል የሚያረጋግጠው የዚህን ምሥጢር እውነትን ነው፡፡

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ «አክሲማሮስ» በተባለው መጽሐፉ «ብቸኛ የሆነው ቅድምናዬ በኃያልነቴና በከሃሊነቴ ይታወቅ ዘንድ ዓለምን ለመፍጠር እፈቅዳለሁ አልኩ» ሲል እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በእርግጥ ለክብሩ መግለጫ እንጂ ለመገልገያ እንዳልሆነ ማረጋገጥ የሚቻለውም እንደ አምላክነቱና ፈጣሪነቱ መጠን እሱ የሁሉ ነገር ምንጭ ስለሆነ የፍጥረቱ የሚፈልገው ምንም ዓይነት ጥቅም ስለሌለ ነው፡፡

## ንብረተ ዓለምና የፈጣሪ ሠራዒ መጋቢነት

### ንብረተ ዓለም

«ንብረተ ዓለም» ማለት «የዓለም ኑሮ ወይም መኖር» ማለት ነው፡፡ ተፈጥሮ የኑሮ መጀመያ ስለሆነ ያልነበረው ዓለም ሲፈጠር ያልነበረው ኑሮም ተጀመረ፡፡ የተጀመረው ኑሮ በጊዜ ተቀመረ፣ በዘመን ተሰፈረ፡፡

## የፈጣሪ ሠራዒ መጋቢነት

ፈጣሪነትን ከእናትና አባትነት ሓላፊነት ጋር ማነጻጸር ይቻላል፤ እናትነትና አባትነት ያሳዳጊነት ግዴታንም የሚያጠቃልል እንደሆነ ሁሉ የተፈጠረውም ዓለም እንዲሁ ያለ ሠራዒ መጋቢ ለራሱ የተተወ አይደለም፡፡ ሁሉም እንደየተፈጥሮ ደረጃው የየራሱን ኑሮ እንዲኖር ከተፈጥሮ ተአምር ያነሰ አይደለም- ፈጣሪ በሠራዒ መጋቢነቱ ለተፈጠረው ዓለም ኑሮና ለአዲስ ተፈጥሮ ክስተት ምክንያት የሆኑ ነገሮች ሁሉ ምክንያትነት ሳይጓደል፣ «በኃይለ ዘርና ምሥጢረ አዝዋግ» የልደትና ሥርፀት፣ የተፈጥሮና ኑሮ ሂደት ሳይቋረጥ፣ የነፋሳት መንፈስ፣ የውኃዎች መፍሰስ፣ የብርሃናት መመላለስ፤ የመዓልትና ሌሊት፣ የክረምትና በጋ መፈራረቅ ሳይታጎል፣ ሁሉም እንደ ተፈጥሮውና የኑሮ ደረጃው የሕገ ተፈጥሮ ተገዥ የሆነው ሥርዓት ሳይፋለስ የየራሱን ዘለዓለም ለመኖር መቻሉ በእርግጥ የሥነ ፍጥረትን ክሥተት ያህል የማያስደንቅ ተአምራዊ ኑሮ ነው፡፡ ከሚከተለው ጥቅስ ስለፈጣሪው ሠራዒ መጋቢነት በቂ ዕውቀትንና ግንዛቤን ማግኘት ይቻላል፡፡

**ቅጥስ**፡ «መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም፡፡» መዝ.103÷36፡፡ «በእሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን፣ እንኖራለንም፡፡» የሐዋ.17÷28፡፡

| | |
|---|---|
| «ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራን እየሠራ ከሰማይ ዝናምን፣ ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፣ ልባችንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም፡፡» የሐዋ.14÷17፡፡ | |
| | «ከእርሱ ልቡን ወደራሱ ቢመልስ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል፡፡» ኢዮ.34÷14፣ 33÷4-18፣ 24÷22 - 24፡፡ |
| «በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፣ ሞትንና ክፋትን፣ በረከትንና መርገምን አስቀምጣለሁ፤ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ መልካምን ምረጥ፡፡» ዘዳ.30÷15-20፡፡ | |

| | |
|---|---|
| | «ዓይኖቼ ነፋሳት በዚህ ዓለም ሳይ ተመጥነው አንዲ ነፍሱ የሚያደርግበትን /ቦታ/ ምሥጢር አዩ።» ሄኖክ 11፣ 16÷17። |

## የሰው ልጅ ተፈጥሮና ኑሮ

የሰው ልጅ በፈጣሪው አርአያና አምሳል የተፈጠረ፤ ሕያዊት፣ ለባዊት፣ ነባቢት ነፍስ ያለችው፣ ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡና የተሰጠው /መቅድመ ወንጌል/፤ መንፈስ አእምሬ፣ መንፈስ ለብዎ፣ መንፈስ ጥበብ፣ መንፈስ ምክር፣ ማንፈስ ኃይል፣ መንፈስ ረድኤት፣ መንፈስ ፈሪሃ እግዚአብሔር ጸጋን በስፋት የታደለ /ኢሳ.11÷1/ ታላቅ ፍጡር ነው። በዚህ ዓይነት ተፈጥሮ «አድርግ አታድርግ» ከሚል አምላካዊ ሕግና ትእዛዝ ጋር ኑሮውን የጀመረ ፍጡር የሰው ልጅ ብቻ ነው፤ ሆኖም በዚህ ዓይነት ኑሮውን የጀመረው የሰው ልጅ ከጊዜ በኋላ እንዳኖሩት አልተገኘም።

**ድቀተ ኃጢአት/ ድቀተ አዳም**

ቀደም ብሎ የተገለጸው ዓይነት ተፈጥሮና ኑሮ የነበረው የሰው ልጅ «አታድርግ» የተባለውን በማድረጉና በክፉ ምኞቱ የዲያብሎስን ዓይነት ስሕተት ስለተሳሳተ የዲያብሎስን ዓይነት አወዳደቅ ወደቀ፤ በዚህ ስሕተቱና ድቀቱም ሁሉንም ዓይነት ሞት ሞተ። ሞተ ኅሊና፣ ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ነፍስ ዘፍ.3÷8-24፣ ሮሜ.12÷15።

<u>ስሕተት</u>፡- «አድርግ፣ አታድርግ» የሚለውን አምላካዊ ሕግና ትእዛዝ መተላለፍ፤

<u>ድቀት</u>፡- ከልዕልና ወደ ትኅትና፣ ከክብር ወደ ኃሣር፣ ከሕይወት ወደ ሞት አዘቅት መውረድ፤

<u>ሞተ ኅሊና</u>፡- የንጽሐ ልቡና እጦት፣ የክፉ አሳብ ተገዥ መሆን፤

<u>ሞተ ሥጋ</u>፡- የነፍስ ከሥጋ መለየትና ወደ አፈርነት መመለስ፤

<u>ሞተ ነፍስ</u>፡- የነፍስ ወደ ሲኦልና ገሃነም መውረድ፣ ከዘለዓለማዊ ኩነኔ /ፍርድ ላይ መውደቅ፤

<u>ምክንያተ ስሕተት</u>፡- ምክረ ሰይጣን፣ ሰይጣናዊ ምኞት እከብር ባይ ልቡና፤

<u>የምክንያት ምክንያት</u>፡- የአንድን ድርጊት ውጤት አስቀድሞ ለማወቅ ያለመቻል ድክመት /ሰብአዊ ድክመት/፤

## ተስፋ ድኅነት፣ ድኅነት፣ ምሥጢረ ድኅነት፣ ምክንያተ ድኅነት

## ተስፋ ድኅነት

የሰው ልጅ ስለፈጸመው ጥንተ አብሶ ከዲያብሎስ ያላነሰ በደል በመፈጸም የዲያብሎስን ዓይነት አወዳደቅ ቢወድቅም እንደ ዲያብሎስ ዕሩቅ ውዱቅ ሆኖ አልቀረም። ማለትም በተፈጥሮ የታደለውን ጸጋ ክብር እንደተገፈፈና የዲያብሎስን አወዳደቅ እንደወደቀ አልቀረም፣ አውቆ በድፍረት፣ ሳያውቅ በስሕተት በሠራው ኃጢአት ክፉኛ ስለተጸጸተ በቃል ኪዳን የተደገፈ ተስፋ ድኅነት ተሰጠው። ይህም የድኅነት ተስፋ «ኪዳነ አዳም፣ ኪዳነ አብርሃም፣ ኪዳነ ኖኅ» በመባል ይታቃል። ኪዳነ ሕይወት፣ ኪዳነ ምሕረት፣ ኪዳነ በረከት፣ ማለት ነው።

ኪዳነ አዳም የሐዋ.3÷19-25፣ ገላ.4÷4።

ኪዳነ አብርሃም የሐዋ.3÷25።

ኪዳነ ኖኅ ዘፍ.9÷8።

## ዘመነ ተስፋ

ከድቀተ አዳም እስከ ክርስቶስ ድረስ ያለው ዘመን የተስፋ ዘመን ይባላል። ዘመነ ክርስትና ራሱ የትንሣኤ ሙታንና የመንግሥተ ሰማያት ተስፈኞች ዘመን እንደመሆኑ መጠን በእርግጥ የተስፋ ዘመን ሊባል ይችላል። ሆኖም የአዲስ ኪዳን ሕዝብ የመንግሥተ ሰማያት ተስፈኛ ለመሆን የበቃው በክርስቶስ በተፈጸመው የድኅነተ ዓለም ተግባር ስለሆነ ዘመነ ተስፋ የሚለው ቃል ትክክለኛ መጠሪያ ሊሆን የሚችለው ከአዳም እስከ ክርስቶስ ለነበረው ዘመን ነው። ኢትዮጵያዊው ደራሲ «ተፈጸመ ተስፋ አበው በማርያም ድንግል፣ ወበቀራንዮ ተተክለ መድኃኒት መስቀል» ሲል የተናገረው ቃል የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ሐቅ ነው። ለዚህም የምስክርነት ቃል ምንጬ ቅዱስ መጽሐፍ መሆኑ ግልጽ ነው። የሐዋ.3÷19፣ ገላ.4÷4 ወዘተ።

## ዘመነ ተስፋና የዘመነ ተስፋ ኑሮ

የተስፋ ዘመን «ዘመነ አበውና ዘመነ ኦሪት» በሚል ሁለት ክፍለ ዘመን ይከፈላል። ሃይማኖተ አበውና ተስፋ አበው በጽኑዕ እምነት ላይ የተመሠረተ ሃይማኖትና ተስፋ ስለሆነ አምልኮተ እግዚአብሔር በሕገ ልቡና ይፈጸም በነበረበት በዚያ ዘመን እንኳ በዘመኑ ነዋሪዎች ላይ ይታይ የነበረው የእምነትና አምልኮ ጽናትና የምግባር ሥምረት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ እለተ ምጽአት ለሚነሡ ምእመናን ሁሉ አብነትነት ያለው ሆኖ የሚኖር ነው።

**ለምሳሌ፡-** የአቤል ምሥዋዕት ሥሙርነት - ዘፍ.4÷2፣ ዕብ.11÷4

-የሄኖክ እምነት አስደሳችነት - ዘፍ. 5÷22፣ ዕብ.11÷4- 7

- የኖኅ እምነት ተስፋ ፍጹምነት - ዘፍ.6÷8፣ 9÷13፣ ዕብ.11÷7፣ ዕብ.11÷7፣ ያዕ.23 ዘፍ.21÷5።

- የኢዮብ ትዕግሥት ፅሁብ ድንቅነት - ያዕ.5÷11

- የአብርሃም እምነትና ምግባር ፍጹምነት - ዕብ.11÷8፣ 17-20፣ ዘፍ.22÷1-10፣ 21÷12፣

- የመልከ ጸዴቅ ክህነት አብነትነት - ዘፍ.1÷10፣ ዕብ.7÷1-4፣ መዝ.109÷4።

- የሣራ ደግነት - ዘፍ.18÷12፣ 1ጴጥ.3÷6

- የርብቃ ትጻር ፈላጊነት - ዘፍ. 24÷58

በዘመነ አሪት ይፈጸም የነበረው የእምነትና አምልኮ ተግባር ከዘመነ አበው ጋር ሲነጻጸር በሕገ ልቡና ይፈጸም የነበረው ሥርዓተ አምልኮ በሕግ መጽሐፋዊና በሥዩማን ካህናት ሠራዒ መጋቢነት እንዲፈጸም ከመደረጉ በቀር የተቀነሰ ወይም የተጨመረ ነገረ ሃይማኖት የለም።

## ድኅነትና ምሥጢረ ድኅነት

«ድኅነት» የሚለው ቃል በአጭሩ የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ያጣውን የተፈጥሮ ጸጋ ክብር በአዲስ ተፈጥሮ እንደገና ለመታደል መብቃቱን ለመግለጽ የሚነገር ልዑል ቃል ነው። በሌላም አገላለጽ ድኅነት የሚለው ቃል አዳም በክርስቶስ የታደለውን የሕይወተ ሥጋና ሕይወተ ነፍስ፣ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ ጸጋ ሉቃ.2÷10፣ ሮሜ.5÷10-21/ ወይም በሌላ አነጋገር የሞተ ሥጋና የሞተ ነፍስ ድቀት የደረሰበት አዳም በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘው /የሐ.20÷3-1/ ትንሣኤና ሕይወት የሚገለጽበት ሕያው ቃል ነው። ዮሐ.11÷25-28። በቀረበው ትንተና ላይ እንደሚታየው ይህ ምሥጢር በብዙ ዓይነት ገጸ ንባብ የተገለጠው የተለያየ ትርጉም ስላለው አይደለም። ሁሉም ዓይነት ገጸ ንባብ ሲተረጐምና ሲመሠጠር የሚያስተላልፈው መልእክት አንድ ነው። በሐዲስ ተፈጥሮ ወደ ጥንተ ተፈጥሮ ደረጃ መመለስ፣ ከብልየት መታደስ፣ በአዲስ ሕይወት የተፈጥሮ ጸጋን መልበስ ወዘተ ነው።

## የድኅነተ ዓለም ተግባር አፈጻጸም

እግዚአብሔር በኪዳነ አዳምና በኪዳነ አብርሃም ለሰው ልጅ የገባው ተስፋ ድኅነት የተፈጸመው በአንድ ልጁ ምሥጢረ ሥጋዌ ሲሆን ወልደ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን

የድኅነተ ዓለም ተግባር የፈጸመውም ሕማሙንና ሞቱን የኃጢአት መደምሰሻ /ማቴ.26÷26-29/ የዲያብሎስና የሞት ድል መንሻ /ኢሳ.26÷10፣ 1ቆሮ.15÷15/፣ የመንግሥተ ሰማያትና የዘለዓለማዊ ሕይወት መውረሻ /ዮሐ.12÷32፣ ዕብ.12÷18-25/ በማድረግ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የፈቀደው ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ሕይወትነት ሞተ ሥጋ በትንሣኤ ሥጋ፣ ሞተ ነፍስ በሕይወተ ነፍስ ተደምስሷል። የዚህ ድኅነት ባለቤት ለመሆን የሚቻለውም በትምህርተ ድኅነት ለሰው ልጅ ሊታደል የሚችልበትን ምሥጢር በመፈጸም የመድኃኒት ቤትነቷን በተግባር በመተርጎም ላይ ትገኛለች።

እግዚአብሔር «የድኅነት አምላክ» ተብሎ የሚጠራው በልጁ ማለትም በክርስቶስ ኢየሱስ በፈጸመው የድኅነተ ዓለም ተግባር ብቻ አይደለም። በኪዳነ ኖኅ /ዘፍ.9÷13/ እንደተገለጠው ከዚያም በፊት ለሰው ልጅ ኑሮ ደኅንነት ይፈጽመው በነበረ የትድግና ተግባር የድኅነት አምላክ መሆኑን ለሰው ልጅ በተግባር ገልጿል። ይህንንም ከሚከተለው ትንተና መረዳት ይቻላል።

# ድኅነት፣ ምሥጢረ ድኅነትና ምክንያተ ድኅነት በዘመነ ብሉይና በዘመነ ሐዲስ

## የዘመነ ብሉይ ድኅነትና ምክንያተ ድኅነት

| ድኅነት | ምክንያተ ደኅነት |
|---|---|
| በዚህ ዓለም ላይ ለመኖር የሚቻልበትን ምክንያት ሁሉ ከሚያሳጣ አባር ቸነፈር /ኢዮ.1÷1-34/ ስደትና ምርኮ /ኤር.1÷1-34/<br><br><u>የነፃነት እጦትና የባዕድ ተገዥነት</u> | - በእምነትና አምልኮ አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ /ዕብ.11÷4-40/<br>-<u>የእምነትና አምልኮ</u> መሥዋዕት አቅርቦት /ዘፍ.8÷2፣ ኢዮ.1÷5/<br>- ጸሎትና ጾም /2ኛ ነገ.20÷26፣ ዮና.2÷5 ኢ.22÷27/፣<br>-ምጽዋት /ዳን.4÷2/፣ እንግዳ ተቀባይነት /ዘፍ.18÷1- 8/፣<br>- እግዚአብሔር እንደፈጣሪነተቱና አምላክነቱ የሚያደርገው |

| | |
|---|---|
| /ኤር.39÷17፣ ዘፀ.2÷7/ ወዘተ ... አደጋ በእግዚአብሔር ረድኤት በመጠበቅ የሕይወት ኑሮ መኖር | ቸርነት /መዝ.102÷18/ |
| **የዘመነ ሐዲስ ድኅነትና ምክንያተ ድኅነት** | |
| **ድኅነት** | **ምክንያተ ድኅነት** |
| • በአዲስ ተፈጥሮ ወደ ጥንተ ተፈጥሮ ደረጃ መመለስ 2ቆሮ.5÷17፣ ኤፌ.4÷24፣<br>• በጥምቀት እንደገና መወለድ ዮሐ.3÷5፣<br>• ከኃጢአት ባርነት ነፃ መውጣት ዮሐ.8÷31<br>• ከማዕሰረ ኃጢአት መፈታት ዮሐ.20÷23፣<br>• ሞተ ሥጋንና ሞተ ነፍስን በትንሣኤና ሕይወት ድል መንሣት ዮሐ.12÷25-34፣ 1ቆሮ.15÷42፣<br>• ከኃጢአት እድፈት መንጻት ዕብ.9÷13፣ ራዕ.7÷15፣<br>•በምድራዊና ሰማያዊ በረከት መባረክ ዮሐ.3÷26፣ | - የክርስትና እምነትና ጥምቀት ማር.16÷16<br>- ምግባር ያዕ.2÷21-26 ማቴ.25÷34-46<br>- ምሥጢረ ቁርባንን መፈጸም ዮሐ.6÷54<br>- ፍቅር 1ዬጥ.4÷6<br>- ጾም፣ ጸሎትና ንስሐ የሐዋ.3÷34፣ የሐዋ.3÷20፣ 8÷22፣ 3÷20<br>- ይቅርታ ማድረግ ማቴ.6÷4፣ 18÷35<br>- ምጽዋት ማቴ.6÷1- 3፣ 19÷21<br>- የቅዱሳን አማላጅነትና በስማቸው የሚፈጸም ምግባረ ሠናይ ማቴ.10÷42<br>- የእግዚአብሔር ቸርነት ሮሜ.2÷4፣ 9÷16፡፡ |

# የክርስቶስ ማንነት

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ለክርስትና እምነት መሠረቱ ይህ ዕውቀት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር እንደሆነ ማወቅ ሕይወት ያለው ዕውቀት ነው፡፡ /ዮሐ.17÷3/፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችውም በዚህ እምነት ላይ ነው፡፡ /ማቴ.16÷16/ ያለዚህ እምነት በጽኑዕ ዐለት ላይ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ባለቤት መሆን አይቻልም፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ ሰው የሆነው በዚህ ሥጋዊ ኃጢአተኛውን ዓለም ለማዳን አስቀድሞ በገባው ቃል መሠረት ነው /ኤፌ.1÷3-9/፡፡

ዕዝራ ሱቱኤል ከእግዚአብሔር ጋር ቃል በቃል ለመነጋገር በበቃበት የራእይ ወቅት እግዚአብሔር ዓለምን በማን ሊጎበኝ እንዳሰበ ለመጠየቅ መቻሉንና ከዚያም

በመልሱ ኀብኙ ራሱ መሆኑንና ይህን ኅብኘት ለማድረግ ፈቃዱ የሆነውም ከፍጥረተ ዓለም በፊት ጀምሮ እንደነበር ለመረዳት እንደቻለ በስሙ የተጻፈው መጽሐፍ ቃል ያረጋግጣል /ዕዝራ.ሱቱኤል 3÷55፣ 4÷4/:: ይህም የሚያመለክተው የክርስቶስ ምጽአት ከጊዜ በኋላ ታስቦ የተፈጸመ ድርጊት አለመሆኑን ነው::

ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ምሥጢረ ምጽአቱን አስቀድሞ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለአባት ተፀነሰ፣ ተወለደ፣ ቀስ በቀስ አደገ፤ በሠላሳ ዘመኑ በማየ ዮርዳኖስ፣ በእደ ዮሐንስ በመጠመቅ የእኛን ጥምቀት ባረከ:: ከዚያም በምድር ላይ በመመላለስ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን ሰበከ፣ አስተማረ፣ ስለእኛ ስለሰዎችና ስለመዳናችን በመስቀል ላይ ተሰቀለ፣ ሞተ በሦስተኛው ቀን ተነሣ፣ በአርባኛው ቀን አረገ፣ በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ላከ፣ ዳግመኛ ለፍርድ እንደሚመጣም በሐዲስ ኪዳን ፍጹም ተስፋ ሰጠ::

## የእምነትና አምልኮ ቀኖና አፈጻጸም በብሉይና ሐዲስ ኪዳን

## በዘመነ ብሉይ

| በዘመነ አበው | በዘመነ ኦሪት |
|---|---|
| - ቀደም ብሎ በተጠቀሰው መንገድ ከፈጣሪ ጋር ግንኙነት በማድረግና የሚፈለገውንም መሪ ቃል በመቀበል የአምልኮ ግዴታን <u>በሕገ ልቡና</u> መፈጸም<br>- በኪዳነ  አብርሃም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የገባው ቃል ኪዳን የሚጠይቀውን ግዴታ በመፈጸም የአብርሃማዊ በረከት ተጠቃሚ መሆን ዘጸ.7÷12-17<br><u>የቃል ኪዳን ግዴታ</u><br>- ጽድቅና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ መጠበቅ ዘፍ.18÷18-26::<br>የአማናዊ ጥምቀት ምሳሌ የሆነውን ሥርዓተ ምሳሌ የሆነውን ሥርዓተ ግዝረት መፈጸም ዘፍ.17÷16:: | - የአብርሃምን እምነትና ምግባር ግዴታ <u>በሕግ መጽሐፋዊ</u> መፈጸም<br>ዘሌ.20÷1-10፣ ዘጸ.6÷17፣ 7÷9-20፣ 8÷1-20::<br>- ሥርዓተ ግዝረትን መፈጸም ዘሌ.12÷2<br>- የአምልኮ መሥዋዕት በማቅረብ በረከትን፤ የኃጢአት ሥርየትን፣ የአረቦን ድኅነትን ወዘተ.. ለማግኘት መብቃት ዕብ.9÷10::<br>- በጸሎት አቅርቦት አምልኮትን በመግለጽ የራስንም ሆነ የሌላውን ደኅንነት ማስጠበቅ 2÷1 ነገ.20÷1-5፣ ዘፀ.32÷11፣ ዘኍ.16÷46::<br>- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዘመነ አበው ቅዱሳን ምእመን የእነሄኖክን፣ አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን፣ ከዘመነ ኦሪት የእነሙሴን፣ ጌዴዎንን፣ ባርቅን፣ ሶምሶንን፣ ዮፍታሔን ስም በመጠቃቀስ ስለ |

| | |
|---|---|
| የአምልኮ መሥዋዕት በማቅረብና በእምነት የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት የአብርሃም በረከት ተሳታፊ መሆን<br>ዘፍ.12÷1- 10፣ 25÷21።<br>- በጸሎት አቅርቦት አምልኮትን መግለጽ<br>ኢዮብ.22÷27፣ 30፣ 17፣ 15÷2፣ 20÷7- 18፣<br>ኢዮ.42÷8። | እምነታቸው ደግነት በምሳሌነት ያወሳል።<br>ዕብ.11÷4-40። |

# አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት

## 1. ምሥጢረ ሥላሴ

<u>ምሥጢረ ሥላሴ</u>፡- እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ነገር ግን ሦስት ገጽ፣ ሦስት አካል አሉት። እነዚህም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። አብ አባት ነው። ወልድ ልጅ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረጸ ነው። ሦስት አካላት አንድ መለኮት ናቸው።

ምሥጢረ ሥላሴ በብሉይ ኪዳን ብዙ ጐልቶ ባይነገርም አልፎ አልፎ በሥነ ፍጥረትና በነቢያትም ታውቋል /ዘፍጥ18፣ ኢሳ.6/። በሐዲስ ኪዳን ግን በምሥጢረ

ሥጋዌ ምሥጢረ ሥላሴ በሚገባ ታውቋል፤ በዮርዳኖስ በደብረ ታቦር /ማቴ.17÷3-17/። በሊቃውንትም ዘንድ በምሥጢረ ሥላሴ የአብ ወላዲነት፣ የወልድ ተወላዲነትና የመንፈስ ቅዱስም ከአብ መሥረጽ በሰፊው ተተርጉሟል። አብ ወላዲ ነው፤ ወልድ ተወላዲ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው። አብ ተወላዲ አይባልም፤ ወልድ ወላዲ አይባልም፤መንፈስ ቅዱስ ወላዲ ተወላዲ አይባልም። ወላዲ፣ተወላዲ፣ሠራጺ የሚባሉት ቃላት ሦስቱ አካላት ለየብቻ የሚታወቁባቸው የግብር ስሞች ናቸው። አንዳንድ ሰዎች አካልና ግብርን ማፋለሳቸው ሳይታወቃቸው «ወላዲ መለኮት፤ ተወላዲ መለኮት ሠራጺ መለኮት» እያሉ መለኮትን ለግብር ስም ይቀጥላሉ። ይህ በትምህርተ መለኮት ትምህርት ስሕተት ነው፤ ግብርን ያፋልሳል።

የአብ መውለድ፣ የወልድ መወለድ፣ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ በዘመን በዕድሜ መቀዳደም የለበትም። በሰው ሕገ ልደት አይመስልም። በምሥጢረ ሥላሴ የሦስቱን አካላት ዕሪና /እኩልነት/ ለማጉላት «ወላዲ መለኮት ተወላዲ መለኮት ሠራጺ መለኮት» እያሉ መለኮትን በአካል ሦስት ማለት የአካልንም የመለኮትንም ፍች አለማወቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ አማልክትን መፍጠር ነው። እንደ አረማውያን ምሥጢረ ናህድናን ለማጕልመስ ሲባል ደግሞ የሦስቱን አካላት ዕሪና /እኩልነት/ መገልጠል ደግሞ እንደ አርዮስ /እንደ ጅሆባውያን/ እንደ መቅዶንዮስ መሆን ነው። ስለዚህ ምሥጢረ ሥላሴን ለመማር ጥንቃቄ ያስፈልጋል። መለኮት /ማልኹት/ በዕብራይስጥ ቋንቋ «መንግሥት» ማለት ነው። በግእዝ ግን «ባሕርይ፣አገዛዝ፣ ሥልጣን፣ አካል» ማለት ነው። መለኮት በአካላት አይከፈልም።

<u>አንድነት</u>፡- የባሕርይ፣ የህልውና፣ የፈቃድ፣ የአገዛዝ

<u>ሦስትነት</u>፡- የስም፣ የግብር፣ የአካል

<u>የስም አንድነት</u>፡- እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ ጌታ

<u>የስም ሦስትነት</u>፡- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ

<u>የግብር ሦስትነት</u>፡- አብ ወላዲ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ

<u>የአካል ሦስትነት</u>፡- ለአብ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ለወልድ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ አለው።

## ጥቅስ ስለ አንድነትና ሦስትነት

## ከመጻሕፍተ ሊቃውንት

- «ሥላሴ በተዋሕዶ፣ ወተዋሕዶ በሥላሴ ሦስትነት በአንድነት፤ አንድነት

በሦስትነት» ሱንትንዮስ ሃ.አ.ም.103፡፡

- «እንዘ አሐዱ ሠለስቱ፣ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ- አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ፡፡» ባስልዮስ ዘቄሣርያ ሃ.አ.ም 113 ክፍል 1
- «ወሶበሂ ንብል እግዚአብሔር ወአሐዱ መለኮት ንብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ - አንድ እግዚአብሔር  አንድ መለኮት ስንል ስለአብ፣ ስለወልድ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ መናገራችን ነው፡፡» ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ሃ.አ.ም.107 ክፍል 1
- «ወአንሰ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ - እኔ እግዚአብሔር ባልኩ ጊዜ ስለአብ፣ ስለ ወልድ ስለ መንፈስ ቅዱስ እላለሁ፡፡» ባስልዮስ ዘአንጾኪያ ሃ.አ.ም 96 ክፍል 1

# የምሥጢረ ሥላሴ ክሥተት

## በዘመነ ብሉይ

- «ንግበር ሰብአ በአርአያነ» ዘፍ. 1÷26
- «አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ» ዘፍ.3÷27
- «ንዑ ንረድ ወንከዓው ነገሮሙ...» ዘፍ.11÷7
- በቤተ አብርሃም .... ዘፍ.18÷1-33
- «ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልዐ ምድረ፣ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንአ ሰማያት ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኩሉ ኃይሎም» መዝ.32÷5
- «ዐቢይ እግዚአብሔር ወዐቢይ ኃይሉ፣ ወአልቦ ኍልቍ ለጥበቢሁ» መዝ.146÷**5**

## በዘመነ ሐዲስ

- «ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ማቴ.28÷19

## 2. ***ምሥጢረ ሥጋዌ***

ምሥጢረ ሥጋዌ፡- ሰው ከፈጣሪው ተጣልቶ ጸጋውን መገፈፉንና ባሕርዩንም ማሳደፉን፣ መቁሰሉን፣ መጐስቆሉን ከተረዳን ዘንድ መድኃኒቱ ምን እንደሆነ እንመልከት፡፡ የሰው ዘር ሁኔታ በየጊዜው ከክፋት ወደ ክፋት ከጥፋት ወደ ጥፋት እየጨመረበት ስለሄደ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ ሰውንም ወደ ቀድሞው ይዞታው ለመመለስ እግዚአብሔር ራሱ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ተወለደ፤ ተሰቅሎ ሙቶ ሰውን ወደ ቀድሞ ቦታው መለሰው፡፡ ይህ የአምላክ እቅድ ማለትም ሰውን ለማዳን ያደረገው ሁሉ አምላካዊ መግቦት ይባላል፡፡ አምላክ ሰው በመሆኑ ሰውም አምላክ ሆነ፡፡ ተዋሕዶውም ሚጠት፣ ውላጤ፣ ቱስሕት፣ ቡዓዴ የለበትም፡፡ ተዋሕዶው የነፍስና የሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌ ነው፡፡ አንድ ሰው ሁለት ባሕርይ እንደማይባል ሁሉ በመለኮትና በሥጋም ከተዋሕዶ በኋላ ሁለትነት የለም፡፡ ከኬልቄዶን የአመጽ ውሳኔ በኋላ በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስን «አንድ አካል ሁለት ባሕርይ» ይሉታል፡፡ ነገር ግን የባሕርይንና የአካልን ፍች ባለመጠንቀቅ «እኔ ብቻ ያልሁት መሆን አለበት የሚል የእልክ ውሳኔ ነው እንጂ ከተዋሕዶ በኋላ ሁለትነትን መስበክ ከንቱነት ነው፡፡ በግሪክኛው «ኤኖሲስ» አንድነት ነው፡፡ «አሐደ» አንድ ማለት ሲሆን «ተዋሕዶ» ማለት አንድ ነው፡፡ በቅድሚያ የቋንቋው አተካከልና የፊደሎች አቀማመጥ በደንብ ሳይጠና ሃይማኖትን ያህል ነገር በችኮላ በመወሰኑ የኬልቆዶን ጉባዔ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ጉባዔ ከለባት /የውሾች ጉባኤ/ እየተባለ ይጠራል፡፡ ከዚህም ጋር ኬልቄዶናውያን ክርስቶስ «ሁለት ፈቃድ ነበረው» ይሉታል፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር አለመስጠት ነው፡፡

## ጥቅስ ትንቢታዊ

«በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ፡፡» በዘፍ.22÷8፣ ሐዋ.3÷19-26፡፡
«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ትንቢትና በብዙ ምሳሌ ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ በዚህ ዘመን ደግሞ ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ተናገረን፡፡ ዕብ.1÷1-3፡፡

## ጥቅስ ብሥራታዊ

«እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን የምሥራች እነግራችኋለሁ፣ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀን እሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና፡፡» ሉቃ.2÷10፡፡

የክርስቶስን ልደት ወይም ትስብእት «ምሥጢር» ያሰኘው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በዳግም ልደት ከእናት ያለ አባት በድንግልና የመወለዱ፣ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የመሆኑ ግብር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ልጅ እናትነት የተመረጠችው ድንግልም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡

የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት የክርስትና እምነት ትምህርት መሠረት ስለሆነ ያለዚህ ትምህርትና እምነት ክርስቲያን መሆንም ሆነ መባል አይቻልም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያመነና የተጠመቀ ይድናል /ማር.16÷16/ ሲል የተናገረውም ይህን እምነት ነው።

## ምሥጢረ ጥምቀት

### የጥምቀት ጠቅላላ አገልግሎት

**ምሥጢር ጥምቀት በዳግም ልደት ማለት በውኃና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዳግመኛ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ። ዮሐ.3÷5።**

ለሥርየተ ኃጢአትና ድኅነት ማር.16÷16፣ የሐዋ.2÷28

ለመንጻትና ለመቀደስ 1ጴጥ.3÷21፣ ቲቶ.3÷5 የሚፈጸም ምሥጢር ነው።

## የጥምቀት ጊዜ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በሌሎችም መሰል አብያተ ክርስቲያናት የሕፃን ጥምቀት የተለመደ ሥርዓት ነው። ሥርዓቱ ሊፈጸም የሚችለውም ከአርባ ቀን ጀምሮ ነው። በዚህ መሠረት ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባ ቀን፣ ሴት ልጅ ደግሞ በተወለደች በሰማንያ ቀን እንዲጠመቁ ይደረጋል። ይህ ቀን ለዚህ አገልግሎት የተመረጠ ቀን ሊሆን የቻለውም ከብሉይ ኪዳን በተወረሰ ባሕል መሠረት ነው። ዘሌ.12÷1-5፣ ሉቃ.2÷21- 24።

በብሉይ ኪዳን ቀኖና አንድ ሕፃን በተወለደ በስምንተኛው ቀን የተገረዘ የብሉይ ኪዳን ሕዝብ አባል በመሆን የአብርሃም በረከት ተሳታፊ ይሆን እንደ ነበር ተጽፏል ዘፍ.17÷7። በዚያ ዘመን ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ሲፈጸም የኖረ ምሥጢር ስለሆነ በዚያው አንጻር አሁንም የሕፃናት ጥምቀት በ40 ቀንና በ80 ቀን በቤተ ክርስቲያናችን ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል።

## የሥርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም

ጥምቀት ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን /ፍ.ነገሥ. አንቀጽ3/፤ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም /ማቴ.28÷19-20/ በውኃ /ዮሐ.3÷5፣ /ፍ.ነገሥ.3/ የሚፈጸም ምሥጢር ሲሆን አፈጻጸሙ በመዝፈቅ ወይም በማፍሰስ /ዲድ.34÷ ፍ.ነገሥ. አ.3/ ሊሆን ይችላል። ሕፃናት ሃይማኖታቸውን ለመመስከር ስለማይችሉ በየጾታቸው የክርስትና አባትና እናት እንዲሰየሙላቸው ይደረጋል።

ጥምቀት አይደገምም /ሮሜ.6÷3፣ ኤፌ.4÷4-7/:: ጥምቀት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምሳሌነት አለው /ሮሜ.6÷3-6፣ ዲድ.34/:: ከጥምቀት በኋላ ማተብ ማሠር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ ሥርዓት ሆኖ ኑሯል:: ስለ ሥርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም በሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በስፋት ተዘርዝሯል::

## 4. ምሥጢረ ቁርባን

ምሥጢረ ቁርባን የክርስቶስን ሥጋና ደም በመብላትና በመጠጣት የዘለዓለም ሕይወትን ለመውረስ የሚቻልበት ምሥጢር ነው:: ዮሐ.6÷54:: በጸሎተ ቅዳሴ ኅበስቱ ወይኑ ተለውጦ በዕለተ ዓርብ ለብዙዎች የኃጢአት ማስተሥረያ በመስቀል ላይ የተሠዋውን የእግዚአብሔር በግ /ዮሐ.1÷29/ አማናዊ ሥጋና ደም ስለሚሆን ይህን መሥጢር ሳያውቅ ወይም ሳያምን ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበል ዕዳ በደል ይሆንበታል:: 1ቆሮ.11÷27- 30::

## 5. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

1. <u>የሙታን ትንሣኤ</u>:- ሰው ከሞተ በኋላ እንደገና ይነሣል:: በነገረ ሃይማኖት ትምህርታችን ይህ ምሥጢር ትንሣኤ ሙታን ይባላል:: ሰው ከፈረሰና ከበሰበሰ በኋላ ይነሣል ስንል እንዲያው በማናውቀው አይደለም:: የተጨበጠ መረጃ አለን:: ይኸውም የክርስቶስ መነሣት ነው:: በኩረ ትንሣኤ ክርስቶስ ባሳየን የትንሣኤ በር ሁላችንም ከመቃብር እንወጣለን፣ የክርስቶስን ትንሣኤ የማያውቁ ሥጋውያን ሰዎች በዚህ ዓለም ብቻ ፈርሰው በስብሰው እንደሚቀሩ አድርገው ስለሚያምኑ የትንሣኤ ተስፋ የላቸውም:: ድካማቸውና ጥረታቸው ሁሉ በዘመን ለሚገታው ለዚህ ዓለም ብቻ ነው:: ፍልስፍናቸው ነገ ስለምንሞት ዛሬ እንብላ እንጠጣ ዛሬ እንደሰት ነገ እንሞታለን የሚል ነው:: ሁለት ዓይነት ትንሣኤ እንዳለ ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል:: ይኸውም የክብርና የውርደት ትንሣኤ ነው:: የክብር ትንሣኤ የሚባለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አክብረው ያረፉ ሰዎች የሚነሡት ነው:: የኀሣር /የውርደት/ ትንሣኤ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያለፈጸሙ ሰዎች የሚነሡት ትንሣኤ ነው:: ስለ ሙታን ትንሣኤ ሌሎች እምነቶች ቢያስተምሩም እንደ ክርስትና ሃይማኖት በቂ መረጃ የላቸውም:: እኛ ግን ፈጣሪያችን ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ድል አድርጐ ስለተነሣ ስለ ትንሣኤ የምንሰጠው ትምህርት እውነተኛ ነው:: የሃይማኖታችንም ቀኖና ፍጻሜው «የሙታንን ትንሣኤ እንጠባበቃለን» የሚል ነው:: ክርስቲያኖች የሥጋን ሞት እንዳይፈሩ ታዘዋል:: ነገር ግን ነፍስና ሥጋ

በትንሣኤ ከተዋሓዱ በኋላ የሚመጣውን ሁለተኛውን ሞት ፍሩ ተብለዋል፡፡ ይህ ሞት ትንሣኤ የማይከተለው ነው፡፡ ይህ ሞት የመጨረሻው ነው፡፡

«የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲህ ነው፤በመበስበስ ይዘራል፤ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፤በክብር ይነሣል፤በድካም ይዘራል፣በኃይል ይነሣል፣»1ቆሮ.15÷42-57፡፡

የሙታን ትንሣኤ በትርጓሜ ቤት ዘይቤ <u>ትንሣኤ ዘጉባኤ</u> ተብሎ ሲጠራ የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ ደግሞ <u>ትንሣኤ ዘለክብር</u> እና <u>ትንሣኤ ዘለኅሳር</u> በመባል ይታወቃል፡፡

«ያንጊዜ ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን፣ ይህ የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ ሞት ድል በመነሣት ይዋጣል፤ መቃብርም እንዲሁ» ኢሳ.26÷19፣ 25÷8፣ ዳን.12÷2፣ ሆሴ.13÷14፣ 1ቆሮ.15÷54-57፡፡

ከዚህም ጋር ያን ጊዜ የሙታን መቀስቀሻ መለከት ሲነፋ በሞት ያንቀላፉው ሁሉ እንደሚነሣ፣ ሌላው ደግሞ ከመቅጽበት ግብር እምግብር እንደሚለወጥ በፍጹም እምነትና ተስፋ ይጠበቃል፡፡ /1ቆሮ.15÷51፣ 1ተሰ.4÷15/፡፡

# ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን

# ክርስቶስ ዘቤተ ክርስቲያን

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በቅዱስ ወንጌሉ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ... ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ ከሆነው አንዳችስ እንኳ ያለ እርሱ የሆነ የለም፤ በእሱ ሕይወት ነበረች፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፤ ብርሃንም በጨለማ ያበራል ጨለማም አላቸነፈውም...ለሰው ሁሉ የሚያበራ እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ፤ በዓለም ነበረ፤ ዓለሙም አላወቀውም.... ቃል ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ.... እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀበልን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና»/ዮሐ.1÷1-17/ ሲል የተናረገው ስለ ክርስቶስ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ በመጀመሪያ «ቃል ነበረ» ሲል ቀዳማዊነቱን፣ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ሲል ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላለው፤ አንድነት፣ «ቃልም እግዚአብሔር ነው» ሲል አምላክነቱን፣ «ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ያለ እሱ የሆነ አንዳች የለም» ሲል ፈጣሪነቱን፣ «በእሱ ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች» ሲል የዓለም መድኃኒትነቱን፣ «ብረሃን በጨለማ ያበራል፤ ጨለማም አላቸነፈውም» ሲል የብርሃንነቱን ኃያልነትና ዘለዓለማዊነት፣ «እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ፣ በዓለም ነበረ፣ ዓለሙም አላወቀውም» ሲል

ምሉዕነቱን፣ «ቃል ሥጋ ሆነ» ሲል ሰው መሆኑን፣ «ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በእኛ አደረ» ሲል ለእኛ ሲል ሰው መሆኑን፣ «እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀበልን፣ በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና» ሲል በእሱ ስላገኘው የድኅነተ ሥጋና ድኅነተ ነፍስ ጸጋ ምልዓት መመስከሩ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን አሁንም ስለ ክርስቶስ የምትመሰክረውን ይህን ቃል ነው።

«ክርስቶስ» ማለት «መሢሕ»፣ «መሢሕ» ማለትም «የተቀባ» ማለት ነው። ይህ ቃል በሌላ አንጻር ሥዩማን እግዚአብሔር ለሆኑ ነቢያትና ካህናት፣ እንዲሁም ነገሥታት ሊነገር የሚችል ቋንቋ ስለሆነ «ክርስቶስ ዘቤተ ክርስቲያን» የሚለው ቃል ሰማያዊውን ከምድራውያኑ ለመለየት የተነገረ ቋንቋ ነው። ወልደ እግዚአብሔር ሰው በመሆኑ «መሢሕ፣ ክርስቶስ» ቢባልም ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጀ፣ የመሠረተና ያጸና የባሕርይ አምላክ ስለሆነ እሱ የቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያንም የእርሱ ናት። እርሱ «ወልድ» ተብሎ እኛን «ውሉድ»፣ እሱ «ክርስቶስ» ተብሎ እኛን «ክርስቲያን» ያሰኘ እርሱ ነው። በአሁኑ ጊዜ ቅዱሳን ምእመናን «በወልድ ውሉድ» «በክርስቶስ ክርስቲያን» ተብለው የሚጠሩት በወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በእርሱ ነው። ከዚህም ጋር ቤተ ክርስቲያን በምሥጢራዊ አነጋገር አካሉ ስለሆነች ወይም በእርሱ ራስነት የተገጣጠመች አካል ስለሆነች /ኤፌ.4÷13-14/ በእርግጥ እርሱ የቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያንም የእርሱ ናት። ቤተ ክርስቲያን «መድኃኒቴ» ብላ የምትጠራውና የምታመልከው ክርስቶስ ወይም መሢሕ እርሱ ነው። ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ «ስለሕይወት» ቃል በመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን፣ በዓይናችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውንም፣ እጆቻችን የዳሰሱትንም.. ከአብ ዘንድ የነበረውን፣ ለእኛም የተገለጠ ውን የዘለዓለም ሕይወት እንነግራችኋለን» /1ዮሐ.1÷6/ ሲል የተናገረለት መሢሕ ክርስቶስ እርሱ ነው።

በሌላም በኩል የውሸት ክርስቶስ ወይም የውሸት መሢሕ ወደ ኋላም ሆነ ወደፊት የተነሣበትና የሚነሣበት ጊዜ እንደነበርና እንደሚኖርም የታወቀ ስለሆነ /ማቴ.24÷24፣ የሐዋ.5÷29-40/ እውነተኛውን ከሐሰተኛው ለመለየት «ክርስቶስ ዘቤተ ክርስቲያን» የሚለው አነጋገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ይኸውም እውነተኛው ክርስቶስ ወይም መሢሕ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ የመሰከረችለትና የምትመሰክርለት ክርስቶስ ወይም መሢሕ ብቻ በመሆኑ ነው። እነሆ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው ይህ ክርስቶስ ነው። በእውነተኛው መሢሕ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያንም እውነተኛ ስለሆነች በእውነት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት።

ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በጥንተ ስሙ «ወልድ፣ ቃል» ወዘተ ተብሎ ሲጠራ በደኃራዊ ስሙ ደግሞ፡-

-በመድኃኔዓለምነቱ - ኢየሱስ ክርስቶስ ማቴ.1÷21

- በንጉሥነቱ - ክርስቶስ /መሢሕ/ ዮሐ.4÷21

- ሰው በመሆኑ - አማኑኤል /እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው/ ማቴ.1÷23 ይላል፡፡

ከዚህም ጋር በግብር ስያሜ፡-

- ብርሃን ዮሐ.1÷9

- ኖላዊ ዮሐ.10÷1-18

- የሕይወት እንጀራ ዮሐ.6÷35

- የሕይወት ውኃ ዮሐ.14÷7-38

- የሕይወት መንገድ ዮሐ.14÷፥

- አልፋና ኦሜጋ ራዕ.1÷17 /የባሕርይ/

-አንበሳ ራዕ.5÷5

- ረቢ /መምህር/ ዮሐ.3÷2

- የእግዚአብሔር በግ ዮሐ.3÷29

- ሊቀ ካህናት ዕብ.9÷11-15 ወዘተ እየተባለ ይጠራል፡፡

# ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ

የቤተ ክርስቲያን በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የታነጸች የክርስትና እምነት ተቋም ናት /ኤፌ. 2÷20/፡፡ መሥራቿም ራሱ ክርስቶስ ነው፡፡ ማቴ.17÷16-19፡፡ ነቢያትና ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን መሠረትነት ሊጠቀሱ የበቁት ለክርስትና እምነት መሠረቱ ስለ ክርስቶስ የተነገረው የነቢያት ትንቢትና የሐዋርያት ስብከት በመሆኑ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን የምተሰብከው ቀደም ብሎ ነቢያት «ይወርዳል ይወለዳል» ሲሉ የተነበዩለትንና በኋላም ሐዋርያት «ወረደ፣ ተወለደ» ሲሉ ምጽአቱን ከነስለምንነቱ የመሰከሩለትን ክርስቶስን ስለሆነ ይህ ትንቢትና ስብከት ለቤተ ክርስተያን የሲኦል ኃይላት ሊያናውጡት የማይችሉ ጽኑዕ መሠረት ሆኖ ይኖራል፡፡

በአንደኛ ደረጃ «ቤተ ክርስቲያን» ተብሎ የሚጠራው የምእመናን ሐዋርያት መሠረት ላይ የተገነባ አንድነት» ስለሆነ «ቤተ ክርስቲያን» መባል ትክክለኛ ነው

/ኤፌ.2÷27/። የዚህ አንድነት ተቋም የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በምሥጢራዋ ዘይቤ «የክርስቶስ ሙሽራ ትባላለች» /ማቴ.9÷15፣ ራዕ.19÷7፣ ኤፎ.5÷32፣ 2ቆሮ.11÷2/።

ቤተ ክርስቲያን የድኅነት ቤት ትባላለች፣ ምክንያቱም በእርስዋ አማካይነት፣ ወይም በእርስዋ ከሚፈጸሙ ምሥጢራት ውጭ ሌላ የክርስትና መርከብ፣ የራኬብን ቤት የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አድርገው የተናገሩ አበው አሉ።

ቤተ ክርስቲያን የእምነት፣ የተስፋና ፍቅር ግንባታ ተቋም ናት። እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው እንዲኖሩ ቃልና የተግባር ትምህርት የሚሰጠው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት ነው። /በፍቅር ኮከብነት ቆሮ.13÷13/። የክርስትና እምነት ተከታዮች የአባልነት መታወቂያቸው ፍቅር፣ የድኅነት ማረጋገጫው ፍቅር ነው /ዮሐ.13÷35፣ 1ዮሐ.3÷14/። «ጳውሎስኒ ተወፈየ ሠለስተ ለቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ወተስፋ ወፍቅር ... » ቅዱስ ያሬድ።

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በክርስቶስ መቶ ሃያ ቤተሰብእ ወይም ደቀመካሙርት ማለት 12 ሐዋርያት፣ 72 አርድዕት፣ 36 ቅዱሳት አንስት አንድነትና ኅብረት ነው። መንፈስ ቅዱስ ይህን መሠረት አጸና፣ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወረደበት ዕለት በዓለ ሃምሳን ለማክበር ለተሰበሰበው ሕዝበ በተላለፈው የቅዱስ ጴጥሮስ ቃለ ስብከት ብዙዎች የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆኑ /የሐዋ.2÷41/። ይህ አንድነት እስከ እስጢፋኖስ ሞት ድረስ እያደገ ከሄደ በኋላ በእስጢፋኖስ ሞት ተበተኑ። አባላቱ ወደ ተለያዩ አኅጉር ስለተሰደዱ ኢየሩሳሌም ላይ እንደ ኩሬ ውኃ በአንድ ቦታ ተገድቦ የነበረው የክርስትና እምነት ትምህርት እንደ መስኖ ውኃ በየአህጉሩ ተሰራጨ።

በተለይ ወደ አንጾኪያ ተሰድደው የነበሩት ክርስቲያኖች አንድነት እየጠነከረ ስለሄደ «ደቀ መዛሙርት ናዝራውያን» /የሐዋ.24÷5/ እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት ምእመናን «ክርስቲያን» ተብለው ተሰየሙ። የሐዋ.11÷26።

የክርስትና እምነት በዓለም ላይ ያደረገውን መስፋፋትና መጠናከር በምሳሌ መግለጽ ቢያስፈልግ ትክክለኛ ተነጻጻሪ ሆኖ የሚገኘው በቅዱስ ወንጌል እንደተገለጠው የሰናፍጭ ዘር ነው። የሰናፍጭ ቅንጣት እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነች የዘር ዓይነት ናት። ሆኖም ከእርሻ ላይ ስትዘራ የወፎች ማረፊያ የሆነች የዘር ዓይነት ናት። ሆኖም ከእርሻ ላይ ስትዘራ የወፎች ማረፊያ ለመሆን እስከምትችል ድረስ ታላቅ ዛፍ ትሆናለች /ማቴ.31÷33/። የቤተ ክርስቲያንም የዕድገት ልክ እንደዚህ ነው። የተነሣችበትንና የደረሰችበትን የዕድገት ደረጃ ዝቅታና ከፍታ ያለማብራሪያ ከምሳሌው መረዳት ይቻላል።

ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ይህን ስፋት ያላት ታላቅ የሕይወት ዛፍ የሆነችው በዝናም ውኃ አይደለም፣ የወንጌል ጠለ ትምህርት የማይለያት የክርስቶስ ተክል ስለሆነች ነው:: ቃለ ወንጌል በተዘራበት ቦታ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ትበቅላለች፣ ዘሪው ጴጥሮስም ይሁን ጳውሎስ ወይም ሌላ የተዘራው ዘር የሚበቅለውና የሚያድገው በእግዚአብሔር አምላካዊ ግብር ነው:: /1ቆሮ.3÷6-9፣ ማር.16÷28/::

ምድር እንኳ ጠቃሚ ፍሬን የምትሰጠው ከላይ በእርሷ ላይ የሚወርደው የዝናም ነጠብጣብ ብቻ አይደለም:: በሁሉም ወራት የምሕረት ዝናምን ከሚለግሳት እግዚአብሔር የተዘራው ለመብቀል፣ የበቀለው ለማደግና ፍሬ ለመስጠት የሚበቃበትን በረከት ስታገኝ ነው:: /ዕብ.6÷7/::

የተዘራው የሚበቅለው፤ የተተከለው የሚጸድቀው በግብር አምላካዊ እንደሆነ ቢታመንም ለምድራዊው የግብርና ተግባር ትጉህ ገበሬ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ለሰማያዊው ግብርናም እንዲሁ ከዚያ የላቀ ትጉህ፣ ታጋሽና ጠንካራ የወንጌል ገበሬ ያስፈልጋል:: የግብርና ትልቁ ተግባር ደግሞ የተዘራውን ሰብል ከአረምና ከተባይ ተጠ ቂነት መጠበቅ ነው::

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መረዳት የሚቻለውም የወንጌል ገበሬዎችንና የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችን ከፍተኛ ተልዕኮ የጠየቀው ቃለ እግዚአብሔርን ወይም ቃለ ወንጌልን የመዝራቱ ተግባር ብቻ ሳይሆን የተዘራውን ቃለ እግዚአብሔር ከሰው ሠራሽ አረምና ተባይ /ኑፋቄ/ ጥቃት የመጠበቁ ተግባር ነበር:: በመሆኑም ከውጭና ከውስጥ የሚያጋጥመውን ፈተና ለመቋቋም ብዙ ደም ፈስሷል፤ ብዙ ገድል ተፈጽሟል፣ ብዙ መሥዋዕትነት ተከፍሏል::

# ስለ ክርስትና እምነትና ሕይወት የተከፈለ መሥዋዕትነት

## በዘመነ ሐዋርያት፣ ዘመነ ሰማዕታትና ዘመነ ሊቃውንት

### ዘመነ ሐዋርያት

«የጌታን ስም የሚጠራ ይድናል እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት ይጠሩታል፣ ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ፣ ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ ካልተላኩስ እንዴት ይሰብካሉ» /ሮሜ.10÷13-15/::

ዘመነ ሐዋርያት የክርስትና እምነት የዓለም ሃይማኖት ለመሆን የበቃበት፣ ሐዋርያዊ ጉዞ በመንፈስ ቅዱስ ተባርኮ የተጀመረበት፣ በጉዞው ውጤታማነት

የሐዋርያት የዓለም ጨውነት የዓለም ብርሃንነት የተረጋገጠበት፣ ዓለም በጥበቡ ሊደርስበት ያልቻለው የድኅነተ ዓለም ምሥጢር በስብከተ ወንጌል ሥርጭት ገሃድ የሆነበት /1ቆሮ.1÷21/ የቃለ ወንጌል ዘርና መከር ወቅት ነው፡፡

ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከታጠቁ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሂዱና አስተምሩ /ማቴ.10÷26/፤ በጨለማ የነገረኳችሁን በብርሃን ተናገሩት፣ በጆሮአችሁ በሹክሹክታ የነገርኋችሁን በሰገነት ላይ ስበኩት /ማቴ.10÷26/» ሲል የሰጣቸውን ትእዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ዓለም ወጡ፤ መልካሙን የምሥራች ዜና አወሩ የሕይወትንም ቃል ለዓለም አሰሙ፤ የዓለምን ጨለማ ለማራቅና አልጫውን ዓለም ለማጣፈጥ የሚቻልበትን የብርሃንነትና የጨውነት ተግባር ፈጸሙ፤ የተኛውን ቀሰቀሱ፤ የሞተውን አስነሡ /ኤፌ.5÷14/፡፡ የነቃውም ዓለም የተነገረውን የምሥራች ቃል ሰማ፤ይድንበተ የነበረውን ስም ተቀብሎ በክርስትና እምነት ተጠራ /የሐዋ.3÷12/፡፡ ቃለ ወንጌል በዚህ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ላይ የተዘራውና ይህ የሕይወት ፍሬ የተመሠረተው እንግዲህ በእነዚህ ሐዋርያት የወንጌል ግብርና ስለሆነ ዘመነ ሐዋርያት ለክርስትና እምነት በእርግጥ ዘመነ ዘርና ዘመነ ፍሬ እንደሆነ በግልጽ ይታያል፡፡

ይህ እንዲህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በዚያ የበረከት ዘመን እንደ ሲሞን መሠርይ ያሉ /የሐዋ.8÷13-24/ ቢጽ ሐሳውያን ወይም መናፍቃን ከውስጥም ከውጭም በመነሣት የክርስትና እምነትን ለመበረዝ፣ ለማደስና ለመለወጥ ያደርጉት የነበረው እንቅስቃሴ ቀላል ስላልነበረ ዘመኑ የፈተና ዘመን እንደነበረ ማወቅ ይቻላል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ «እኛ ከሰበክንላችሁ ወንግል የሚለይ ትምህርትን ከሰማይ መልአክ እንኳ ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» /ገላ.8÷18/ ሲል በመረረ ቃል ያስጠነቀቀውም ስለዚህ ነበር፡፡

## ዘመነ ሰማዕታት

ዘመነ ሰማዕታት የክርስትና እምነት ተከታዮች እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትነው የእምነታቸውን ደግነት በተግባር ያረጋገጡበት የገድልና ትሩፋት ዘመን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ገድል ፈጻሚ መሆን የጀመረችውም ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ መሆኑ አይካድም፡፡

ለምሳሌ በሐዋርያነት ከተሾሙት ሰባት ዲያቆናት አንዱ የነበረው እስጢፋኖስ በክርስትና እምነት ተቃዋሚዎች በድንጋይ ተደብድቦ የሰማዕትነትን ገድል የፈጸመው በዘመነ ሐዋርያት ነው /የሐዋ.54÷60/፡፡ ሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ <u>ቀዳሜ ሰማዕት</u> ተብሎ ለመጠራት የበቃውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ቀጥሎም

ሐዋርያው ያዕቆብ በአረማዊው ሄሮድስ ትእዛዝ በሰይፍ ተሰይፎ የሰማዕትነትን ጽዋ የተቀበለው በዚያ ዘመን መሆኑ ግልጽ ነው /የሐዋ.12÷2/:: ነገሩ እንዲህ ሲሆን ታዲያ ዘመነ ሰማዕታት ከዘመነ ሐዋርያት የተለየ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ የቻለው በክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ አጠቃላይ ጥፋት አዋጅ ለታወጀበትና አዋጁ ተግባራዊ ለሆነበት ልዩ የሥቃይ ወቅት ይህ ስያሜ እንዲሰጠው ስለተደረገ ነው:: ለዚህ ኢሰብአዊ አዋጅ የታሪክ ተጠያቂ የሆነውም ሮማዊው ቄሣር ዲዮቅልጥያኖስ ነው::

ሆኖም ድርጊቱ በሰላም ዘመን ሊፈጠሩ የማይችሉ አያሌ ሰማዕታት መገኘት ምክንያት ከመሆኑ በቀር በክርስትና እምነት ሂደት ላይ የፈጠረው መሰናክል አልነበረም:: አስቀድሞ እንደተገለጠው ይህ ዕልቂት በይበልጥ ተግባራዊ የሆነው ከ276 /እ.ኤት.አ/ ወይም ከ284 /እ.ኤ.አ/ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ስለሆነ ይህ ወቅት ዓመተ ሰማዕታት በመባል ለሚታወቀው የዘመን አቆጣጠር የታወቀ መነሻ ሆኖ ይገኛል:: ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የክርስትና እምነት ምን ያህል መሥዋዕትነት የተከፈለበት ሃይማኖት መሆኑን ነው::

## ዘመነ ሊቃውንት

ዘመነ ሊቃውንት በክርስቶስ የተነገረውና በሐዋርያት የተሰበከው ቃለ ወንጌልም ሆነ የድኅነተ ዓለም ተግባር አፈጻጸም በስፋትና በጥልቀት የተመሠጠረበት፣ የነገረ ሃይማኖት ቀኖና በዓለም አቀፍ ጉባኤ የተደነገገበትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት መልክና ቅርጽ እንዲኖረው የተደረገበት ሌላው የቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመን ነው::

ይህ እንዲህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ዘመን የመናፍቃን መፍለቂያ ዘመን በመሆኑ ሌላው ዘመነ ሰማዕታት መሆኑ አልቀረም:: ለመሳሌ ቀደም ብለው ከተነሡት ቢጸሐሳውያን ማለት ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ተፈጥሮና ምሥጢረ ሥጋዌ የተሳሳተ እመነትን ይከተል ከነበረው የመናፍቃን አለቃ ሲሞን መሠርይ /በዘመነ ሐዋርያት የነበረ/ ከአምሳያ ተከታዩ ማኒ /በ216 ዓ.ም የተወለደ/ እንዲሁም ሌሎች አሥራው መናፍቃን በኋላ ስለፈጣሪ አንድነትና ሠራዒ መጋቢነት ምሥጢር፣ ስለ ክርስቶስ ሥጋዌና መሥጢረ ድኅነት አፈጻጸም ተግባር የተሳሳተ እምነትና ትምህርት የነበረው ቀንደኛ መናፍቅ መርቅያን /በ160 ዓ.ም የተነሣ/፣ «አንድ አካልና አንድ ገጽ» በሚል ኑፋቄ የምሥጢረ ሥላሴን እምነትና ትምህርት ለማፋለስ የሞከረው አደገኛ መናፍቅ ሰባልዮስ /በ3ኛው መቶ ክ.ዘ/ የቃልን ቅድምናና እንዲሁም በአማናዊ ተዋሕዶ

ሰው የመሆኑን ምሥጢር የካደው ጳውሎስ ሳምሳጢ /በ3ኛው መቶ ክ.ዘ/ «ለፌ እማርያም ክዋኔሁ ለወልድ» ብሎ የተነሣው መናፍቅ ፎጢኖስ /በ4ኛው መቶ ክ.ዘ/ በታወቀ መሰሐቲነቱ «ከአርዮስ በፊት የነበረ አርዮስ» የሚል ስያሜ የተሰጠው መናፍቅ ሉቅያኖስ /በ311 ዓ.ም የሞተ/፤ «ወልድ ፍጡር» ብሎ የተነሣው አርዮስና /ከ257-336 ዓ.ም/ «መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ» በሚል ክሕደት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማናጋት የሞከረው መቅዶንዮስ /463 ዓ.ም የሞተ/ «ኀየንተ ነፍስ ወልቡና ኮኖ መለኮቱ» በሚል ኑፋቄና ለሥጋ ህላዌም ቅድምና ይጥር የነበረው አቡሊናርዮስ/ ከ310- 390/፤ «ሕስወኬ ትሰመይ ወላዲተ ወላዲተ አምላክ አላ ወላዲተ ሰብእ»በሚል ኑፋቄ የእመቤተያችን ቅድስት ድንግል መርያምን ወላዲተ አምላክነት ክዶ ለማስካድ የተነሣው ንስጥሮስ /ዘመነ.ሢመቱ. 428-431/፣ የውላጤ ኑፋቄ መምህር የነበረው አውጣኬ /በ447 ዓ.ም የተነሣ/፤ ሌሎችም መናፍቃን በየተራ የተነሡት «ዘመነ ሊቃውንት» ተብሎ በሚጠራው ክፍለ ዘመን ስለሆነ በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ጉዳት በዘመነ ሰማዕታት ከደረሰው የሚያንስ አልነበረም፤ ይኸውም በዘመነ ሰማዕታት ከደረሰው አንድነትና ኅብረት፣ ሰላምና ፍቅር በዘመነ ሊቃውንትም ሊቀጥል ባለመቻሉ ነው:: የሃይማኖት መለያየት ለቤተ ክርስቲያን ከሁሉም ነገር የሚከፋ ከሆነ ዘመነ ሰማዕታት ቢባል ማጋነን አይሆንም::

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ክፍለ ዘመን ይህ ዓይነቱ ኑፋቄ የተከሠተበት አስቸጋሪ ወቅት የሆነውን ያህል እንደ እነቅዱስ አትናቴዎስ /295-375/፣ እለእስክንድሮስ /312-328/፣ ቅዱስ ቄርሎስ /ከ375-444/፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ /370-379/፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ /329- 389/፣ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ /370-395/፣ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ /ዘመነ ሢመት ከ444-454/፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ /347-407/ ወዘተ ያሉ የመናፍቃን መምቻና የቤተ ክርስቲያን ራስ መመከቻ የሆኑ ሊቃውንት የተነሡበት መልካም ዘመን ነው:: እነዚህ ቅዱሳን አበውና መሰሎቻቸው በሃይማኖት ትምህርት አዕማድነታቸው ዘመናቸውን «ዘመነ ሊቃውንት» ያሰኙ የቤተ ክርስቲያን ከዋክብት በመሆናቸው የክርስትናው ዓለም ይኮራባቸዋል::

## በዘመነ ሊቃውንት የመናፍቃንን ትምህርት ለመቃወምና ሃይማኖትን ለማጽናት የተካሄዱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት

## 1ኛ. <u>ጉባኤ ኒቅያ</u>

- ስጉባኤው መካሄድ ምክንያት የሆነው ኑፋቄ- «**ወልድ ፍጡር**» የሚል፣
- መናፍቁ - አርዮስ፣
- የጉባኤው ሊቀ መንበር - እለእስክንድሮስ፤
- የተሰብሳቢዎች ብዛት - 318፤
- ጊዜው - 325 ዓ.ም፤
- የዘመኑ ንጉሥ - **ቆስጠንጢኖስ**፣
- ***የጉባኤው ውሳኔ - የክርስቶስን አምላክነት በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ማረጋገጥ /ዮሐ.1÷1-4/ «ወልድ ፍጡር» ሲል የተነሳውን ቀንደኛ መናፍቅ አርዮስን አውግዞ መለየት፤***
- ***የጉባኤው የጸሎተ ሃይማኖት ቀኖና - «ነአምን በአሐዱ አምላክ» ከሚለው ጀምሮ «ወነአምን በመንፈቅ ቅዱስ» እስከሚለው ድረስ ድረስ ያለው ክፍል፡፡***

## 2ኛ. <u>ጉባኤ ቁስጥንጥንያ</u>

- ስጉባኤው መካሄድ ምክንያት የሆነው ኑፋቄ - «***መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ***» የሚል
- መናፍቁ - መቅዶንዮስ፤
- የተሰብሳቢዎች ብዛት - 150 ሊቃውንት
- ***የጉባኤው ሰብሳቢ - ጢሞቴዎስ ዘእስክንድርያ፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፤ ኔክታርዮ ዘቁስጥንጥንያ፣ በየተራ፣***
- ጊዜው - 381 ዓ.ም፤
- የዘመኑ ንጉሥ - ቴዎዶክስዮስ
- የጉባኤው ውሳኔ - የሥላሴን መዓርገ መንግሥት የማበላስጥ ኑፋቄ አመንጭ የሆነውን መቅዶንዮስን አውግዞ መለየት፤
- የጉባኤው የጸሎተ ሃይማናት ቀኖና - «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ» ከሚለው በላይ ያለው ቃል፡፡

## 3ኛ. ጉባኤ ኤፌሶን

- ስጉባኤው መካሄድ ምክንያት የሆነው ኑፋቄ - «ሕስወኬ ትስመይ ወላዲተ አምላክ አላ ወላዲተ ሰብእ» የሚል፤
- መናፍቁ - ንስጥሮስ፣
- የጉባኤው ተሰብሳቢዎች ብዛት - 200 ሊቃውንት፤

- የዘመኑ ንጉሥ - ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ፤
- የጉባኤው ውሳኔ- የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት ክዶ ለማስካድ የተነሣው ንስጥሮስን አውግዞ መለየት፤
- የጉባኤው የሃይማኖት ቀኖና - «በአማን ወላዲተ አምላክ» የሚል።

በሌሎች የእምነት ድርጅቶች አራተኛ ጉባኤ እየተባለ የሚጠራው የኬልቄዶን ጉባኤ ሲሆን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ጉባኤ በዓለም አቀፍ ጉባኤነት አይቀበሉትም። ይህ ጉባኤ በአንድነት ጸንታ ትኖር የነበረችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን «ሁለት ባሕርይ» በሚል የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ልዩነት ከሁለት የተከፈለችበት አሳዛኝ ጉባኤ ነው። በመሆኑም ታዋቂው የተዋሕዶ ሃይማኖት መምህር ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የዚህን ጉባኤ ውሳኔ በመቃወም በአደረገው መከላከል ብዙ ፈተና ደርሶበታል።

## ዘመነ ጻድቃን

«ጻድቅ፣ ጻድቃን» የሚለው ቃል ለሁሉም ዓይነት የክርስትና እምነት ቅዱሳን ሁሉ የሚሰጥ የወል መጠሪያ ቢሆንም ይህን ቃል በስምነት ጭምር የሚጠሩበት ግን ከዚህ ዓለም ተድላ ደስታ ርቀው፣ ጾዋ ጥሰው ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሰው ጤዛ ልሰው፣ድንጋይ ተንተርሰው፣ የላመ የጣመ ሳይቀምሱ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብሱ፤ «እኖር ባይና - እከብር ባይ ልቡና» በሚያሠራው ኃጢአት ሰውነታቸውን ሳያሳድፉ የሚኖሩ ግልጽና ሥውር መናንያን ናቸው። የዚህ ዓይነቱ የምናኔ ኑሮ በአብነትነት የሚጠቀሱት አበውም አባ ጳውሊ /ከአባ እንጦንስ በፊት/፣ አባ እንጦንስ /251- 356/፤ አባ ጳኩሚስ /290- 346/፣የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያምና ሌሎችም ናቸው። በአባ ጳኩሚስ የተጀመረው ምናኔ በአባ እንጦንስ አሁን ያለው የምንኩስናና የገዳማዊ ኑሮ ይዘትና ቅርጽ እንዲኖረው ሲደረግ በአባ ጳኩሚስ ደግሞ ገዳማዊው የምናኔ ኑሮ እስከ አሁን ድረስ ጸንቶ ለመኖር በበቃው ሥርዓተ ገዳም እንዲመራ ተደረገ።

ይህም ሲባል በመልካም የኑሮ ደረጃ ላይ ወይም በብልጽግና ኑሮና በዘውድ ሥልጣን ላይም ሁነው በዚህ ዓለም ጥቅምና ድሎት «ልብሳቸው ሳያድፍ ስማቸው ሳይጎድፍ» /ራዕ.7÷13-15/ ክፉውን ሁሉ አቸንፈው በዓለም ላይ የምናኔ ዓይነት ኑሮ የሚኖሩ እልፍ አዕላፍ ምእመናን የሉም ማለት አይደለም።

ከክርስትና እምነት ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ምናኔ በእርግጥ በሐዋርያት፣ በሰማዕታት፣ በገዳማውያን ባሕታውያን፣ በዓለማውያን ምእመናን ሕይወት የታየና የሚታይ ክርስቲያናዊ ጠባይ ስለሆነ የግድ ገዳማዊነትን የሚጠይቅ ውሱን ገድል አይደለም፡፡

ስለሆነም በየትኛውም ጊዜና ቦታ የክርስትና እምነት የሚጠይቀውን ዓይነት ኑሮ በመኖርና በዚያም ለፍጹምነት ኑሮ የሚያበቃ ገድል ትሩፋት በመፈጸም መናኒ ጻድቅ ወይም ፍጹም ክርስቲያን መሆን ይቻላል፡፡ ባለ ቅኔው እንዲህ ሲል እንደተናገረ «እስመ አባ ተአምር ባቲ፣ ገረገራ ዋልድባ ይእቲ»፡፡ ይህ ከሆነ ዘንድ ማንኛውም ዘመን የዚህ ዓይነት ኑሮ ኗሪዎች የሚበዙበት መልካም ዘመን ከሆነ «ዘመነ ጻድቃን» ሊባል ይችላል፡፡

ገዳማውያን መናንያን በብዛት የተነሡት በዘመነ ሊቃውንት ስለሆነ ይህ ዘመን <u>ዘመነ ጻድቃን</u> ይባላል፡፡ ሆኖም የክርስትና እምነት በየጊዜው የሐዋርያትን፣ የሰማዕታትን፣ የሊቃውንትን፣ የመናንያንን መኖር የሚጠይቅ የገድልና ትሩፋት እምነት ስለሆነ ዘመነ ሐዋርያት፣ ዘመነ ሰማዕታት፣ ዘመነ ሊቃውንት፣ ዘመነ ጻድቃን /መናንያን/ መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ ያለው ዘመን አይደለም፡፡ በዚህ ትረካ ለመጠቆም የተፈለገውም መጀመሪያውን እንጂ መጨረሻውን አይደለም፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እንደ ርግብ የዋህ፣ እንደ እባብ ብልህ ሁኑ» /ማቴ.10÷16/ ሲል እንደተናገረው ሁሉንም ዓይነት ገድል መፈጸም የሚቻለው ደግሞ የትኛውም ጊዜ የሚጠይቀውን ጥበብ ከየዋህነት ጋር በመላበስ እንጂ ከእነዚህ ነገሮች ባዶ በሆነ ሰውነት አይደለም፡፡

# ነገረ ማርያምና ነገረ ቅዱሳን

## ሀ. ነገረ ማርያም

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በንጽሕና፣ በቅድስና በሞገስና በጸጋ በክብር የሚመስላትም ሆነ የሚያህላት የሌለ፣ እናትነትን ከድንግልና አስተባብራ የያዘች፤ ከሆነ ጀምሮ በአዳም ልጅነቷ ምክንያት ንጽሐ ጠባይ ያላደፈባት፤ በዚህ ዓለም ኑሮዋም ከሀልዮ ከነቢብና ከገቢር ኃጢአት ንጽሕት የሆነች፤ ከቅዱሳን ሁሉ በላይ ጸጋን የተሞላች፣ ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች፣ በአማላጅነቷ የምእመናን ሁሉ መማጸኛ የሆነች የአምላክ እናት ናት፡፡ /ሉቃ.1÷27-30፣ሕዝ.44÷3-5፣መኃ.4÷7፣መዝ.132÷13፣ ኢሳ.7÷14/

**ስለ ንጽሕናዋ፡** ቴዎዶጦስ /ሃይ.አበ.ም.53÷22/

**ስለ ክብሯ ታላቅነት፡** ዮሐንስ አፈወርቅ /ሃይ.አበ.ም.28÷36-39/ እና ሌሎችም አበው የተናገሩትን ይመለከቷል፡፡

በዚህ ምክንያት፡-

- ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ
- ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር
- እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ እመ እግዚአብሔር
- ሰአሊተ ምሕረት
- ድንግል በክልኤ
- ቅድስተ ቅዱሳን
- መትሕተ ፈጣሪ መልእልተ ፍጡራን ወዘተ.... እየተባለች ትጠራለች፤ ለዚህም ምንጩ የወንጌል ውዳሴ ማርያም ነው፡፡ ሉቃ.1÷26-55፣ ዮሐ.19÷25-28፡፡ ቅዳሴ ያዕቆብ ዘስሩግ፡፡

የታወቀው የቅዳሴ ማርያም ደራሲ አባ ሕርያቆስ «ወስሉጥ ስመኪ በኀበ እግዚአብሔር» ሲል እንደተናገረው የኢትዮትያ ቤተ ክርስቲያን ለእመቤታችን የተሰጠ ው ቃል ኪዳንና ክብር ከሁሉም ቅዱሳን በላይ መሆኑን ታምናለች፣ ታስተምራለች፤ በመሆኑም በማንኛውም ጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ስሟ በተማኅጽኖ ይጠራል፡፡ ከዚህም ጋር በኢትዮጵያም ሆነ በሌላው የክርስትና ዓለም በጸሎትም ሆነ በትምህርት ስሟ ሳይጠራ የሚውልበት ዕለት የለም፡፡

## ለ. ነገረ ቅዱሳን

መላእክት ፣ አበው፣ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቅዱሳን ተብለው ይጠራሉ፡፡ ዘሌ.9÷2፣ 1ጴጥ.1÷15፣ ዮሐ.17÷16፡፡

**ለ.1 የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት**

- ስለሰው ልጅ ሕይወት መላላክ /ዕብ.1÷14/
- እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ማመስገን /ራእ.4÷8-11/
- የሰውን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማድረስ፣ ለሰው ልጅ ምሕረት መለመን /ዳን.9÷20፣ ሉቃ.1÷13፣ ዮሐ.10÷3-5/
- የሰውን ነፍስ ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ /መ.ሱቱ.6÷6-20/
- ፍጥረተ ዓለምን፣ የሰውን ልጅ መጠበቅ /ማቴ.18÷10፣ ዳን.4÷13/
- ለምሕረትም ለመዓትም መላክ /ሮሜ.9÷22/
- በመከራና በችግር ጊዜ ለተራዳኢነት መላክ /ዮሐ.12÷7-11/

- በፍጻሜ ዘመን ኃጥአንን ከጻድቃን መለየት /ማቴ.24÷31፣ ራዕ.7÷14/

## ለ.2 የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት

ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ጸሎታቸውም፣ ምኞታቸውም፣ ደስታቸውም፣ የሰው ልጅ ድኅነት ነው። ዘፍ.48÷16፣ ዳን.10÷10፣ ሉቃ.1÷13፣ ይሁዳ.9፣ ዘካ.1÷12 ዘጸ.23÷20 መዝ.33÷7።

## ለ.3 ክብረ ቅዱሳን መላእክት

ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበሩና ባለሟልነትንም ያገኙ ቅዱሳን በመሆናቸው በሰውም ዘንድ የተከበሩ ናቸው። ስለሆነም የአክብሮት ስግደት ይሰገድላቸዋል። በስማቸው ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽም ይደረጋል። ዳን.8÷15-18፣ ዘፍ.22÷31፣ ዘኍ.22÷31፣ ኢያ.5÷13።

## ለ.4 ስለ ቅዱሳን ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት ጻድቃን፣ ክብር

እነዚህ ቅዱሳን የየራሳቸው ተልዕኮ በገድል በትሩፋት የፈጸሙ ቅዱሳንና ቅዱሳት በመሆናቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ክብር አላቸው የቃል ኪዳን ቅዱሳን በመሆናቸውም ምእመናንን በስማቸው ወደ እግዚአብሔር ይማጸናሉ፤ እነርሱም በዐጸደ ነፍስ ይማልዳሉ። /ማቴ.10÷42፣ ዘጸ.32÷2-15፣ ሄኖክ.12÷33-40/። በነፍስ ሕያዋን ስለሆኑ /ሉቃ.20÷37-40/። በዚህ ምክንያት የአክብሮት ስግደት ይሰገድላቸዋል፤ እግዚአብሔር የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው ስለሆኑ /ራሆ.3÷9/።

# ማጠቃለያ

የሃይማኖት ትምህርት ፍሬ/ውጤቱ/ የእምነት፣ የተስፋ፣ የፍቅር ፍጹምነት ስለሆነ ይህ ውጤት የማይታይ ከሆነ ትምህርቱ በመልካም ምድር ላይ የወደቀ ዘር አልሆነም። በኢትዮጵያ ሕዝብ ልቡና ላይ የወደቀው ቃለ እግዚአብሔር በመልካም ምድር ላይ የወደቀ ዘር ስለሆነ ፍሬው እነሆ የተትረፈረፈ ሆኖ ይታያል። ሆኖም ባማረው የስንዴ ማሳ ላይ እንክርዳድ እንዳይዘራበት ንቁና ትጉኅ የወንጌል ገበሬ ሆኖ መኖር ከቤተ ክርስተያኒቱ የሃይማኖት መምህራን የሚጠበቅ ግዴታ ይሆናል ይህም ምን ጊዜም ቸል ሊባል የማይገባው ኃላፊነት ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር። አሜን።

/ይቆየን/

/ተጨማሪውን ክፍል በቀጣይ እናቀርባለን/